# በበሕቅ ልሕቀ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ

# በየጥቂቱ (ጥቂት በጥቂት) አደገ በ፴ዓመቱ በዮርዳኖስ

# ተ ጠ መ ቀ ።



ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀና መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል እንዳረፈበት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት በታሪክ ድርስትና ስብከት

ክፍል ተዘጋጅቶ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ፡ ም፡

www.ethiopianorthodox.org

# በበሕቅ ልሕቀ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ
# በየጥቂቱ (ጥቂት በጥቂት) አደገ በ፴ዓመቱ በዮርዳኖስ
# ተ ጠ መ ቀ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴፮ኛው ዘመነ መንግሥት
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትረያርክ በሆኑ በ፰ኛው ዓመት በ፲፱፻፶፰ ዓ፣ ም፣
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት በታሪክ ድርሰትና ስብከት
ክፍል ተዘጋጅቶ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ፡ ም፡

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ

www.ethiopianorthodox.org

# መ ግ ለ ጫ ፤

ይህ ዓመታዊ መጽሔት ተወዳጅነትና ተናፋቂነት ያለው ብሔራዊ የቤተ ክርስቲያናችን ባሕል በጉልህ የሚታወቅበትን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደትና የጥምቀት በዓል ታሪክ በመግለጽ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ድርሰትና ስብከት ክፍል በየዓመቱ እየታተመ የሚመጣው በበዓለ ጥምቀቱ አከባበር ላይ የሚገኙ ምእመናን ሁሉ አኊብበው ሥርዓተ ጥምቀቱን እንዲረዱ ለማድረግ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ም ዕ ራ ፍ ፩ ።

# ስለ መሢሕ መምጣት የነቢያት ትንቢት ።

ወደፊት የሚሆነውን ወይም የሚመጣውንና ጊዜው ሲደርስ የሚፈጸመውን ነገር ገና ከመድረሱ በፊት የማወቅ ዕድልና ስጦታ ትንቢት ይባላል ። በዚህ ቃል የሚጠቀሙበት መጻእያትን (ወደፊት የሚፈጸሙትን ነገሮች) ሁሉ አስቀድመው አውቀው በእንደዚህ ያለው ዘመን ውስጥ እንዲህ ይሆናል ብለው ትንቢት የሚናገሩትም አዋቂዎች ነቢያት ተብለው ይጠራሉ ። ትንቢትም ሲባል በሁለት ረድፍ የተመደበ ነው፤ ይኸውም ፩ኛ በእግዚአብሔር መንፈስ ለሰው ልጆች የሚገለጽ እውነተኛ ተንቢትና ራዕይ ።

፪ኛ ፤ ለጥቅም ፍላጎት ጸላእያነ ሠናያት ከሆኑ ልዩ ልዩ ረቂቃን መናፍስት የሚገኝ ሐሰተኛ ትንቢት ማለት ነው ። አዎ ብዙዎች ሐሰተኞች ጠንቋዮችና አሟራቾች፥ ቃልቾች (ቃላተኞች) ኮከብ ቆጣሪዎችና መጽሐፍ ገላጮች ነን ባዮች ሁሉ ወደፊት የሚሆነውን ነገር እናውቃለን ፤ በእንደዚህ ያለ ዘመን ረኃብ ወይም ጦርነት ይሆናል ፤ በእንደዚህ ያለ ዘመን ደግሞ እንዲህ ያለ ነገር ከሰማይ ይወርዳል እንዲህ ያለው ስር ወይም ቅጠል ወይም ይህን የመሰለው ዶሮ ፤ ፍየል ለምሳሌ አዳል በግ ፤ ቡሐ በግ ፤ ወሰራ ፤ ጥቁር ዶሮ ፤ ከሰልማ ፍየል ፤ ለእንደዚህ ያለ ነገር ይበጃል ይህ ካልሆነ ግን እንዲህ ያለ ቅሥፈት ልክፍትና ሕመም ይመጣብሃል እያሉ በሐሰት ተጠቅመውበታል ።

እርግጥ ነው ከዚህ ሁሉ ዓይነት ውስጥ በሳይንስ ምርምር የታወቀው የሳይኮሎጂ ማለት የሰው ነፍስና ጠባይ ምርመራ ጥናትና ትምህርት መኖሩን አንዘነጋም ። ነገር ግን አብዛኛው በጥቅም ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከእውነቱ ይልቅ ሐሰቱ ጐልቶ ይታያል ። እውነተኛው ትንቢት ግን እንደዚህ አይደለም ።

የእውነተኛው ትንቢት መገኛው ራሱ እግዚአብሔር ነው ። ክፉም ሆነ ደግ ወደፊት የሚሆነውን ማናቸውንም ነገር በሕልም ወይም በራዕይ ተገልጾለት ከእግ አብሔር የተሰጠውን ቃል ብቻ የሚናገርና ምንም ዓይነት ሥጋዊ ጥቅም ሳይፈልግና አላውያን ነገሥታትና መናፍቃን ከክብሬ ያዋርዱኛል ፤ የሰው ፊት ይገርፈኛል ብሎ ሳይፈራ ፥ ሳያፍር ሕይወቱን መሥዋዕት እስከ ማድረግ ደርሶ ፥ በተቀደሰ ድፍረት የሚናገር ሰው እውነተኛ ነቢይ ነው ።

በእርግጥ ይህ ዓይነት እውነተኛ ትንቢት በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ለሕዝብም ለአሕዛብም ማለት ለምድር ነገዶች ሁሉ ምንም ዓይነት የማኅበራዊ ኑሮ ልዩነት ሳያደርጉ በግልጽ ተናግረው በግልጽነት የታወቀውን ፍጻሜ ያስገኙና የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነትና ትክክለኛነት አጕልተው ለማሳየት ምርጥ ዕቃዎች ሆነው የተገኙ ነቢያቶች እንደነበሩና አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ለሚፈቅደው ተግባር እንደነዚሁ ያሉትን ነቢያት ማስነሣት እንደሚችል አያጠራጥርም ።



እግዚአብሔር ለነቢይነት የሚመርጣቸው ሰዎች ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ የተቀደሱ ልበ ንጹሖችና በመልካም ሥነ ምግባር የተጌጡ ፥ ከክፉ ነገርም ሁሉ የራቁና የተጠበቁ መሆን እንዳለባቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጿል (ኤር ፩፡ ፭ ።

እንግዲህ ክርስቶስ (መሢሕ) ወደዚህ ዓለም መጥቶ ፥ ከሥጋችን ሥጋ ፤ ከነፍሳችን ነፍስ ነሥቶ አምላክ ወሰብእ ሆኖ ማለት ተዋሕዶ በኃጢአት ጨለማ የተዘጋውን የዓለም ሕዝብ ወደ ብርሃን መልሶ በትምህርተ ወንጌሉ የመንፈስ ሰላምና ነፃነትን ዐውጆ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተጋረደውንም የጥል ግርግዳ (ዓረፍተ ጽልእ) አፍርሶ እርቅ እንዲመሠረት ልጅነት እንዲሰጥ እግዚአብሔር ባሳደረባቸው መንፈሰ ረድኤት እየተመሩ በሕልምም ሆነ በራእይ እየተገለጸላቸው ትንቢት የተናገሩና የቃሉም እውነተኛነትና ትክክለኛነት ፍጻሜው ወይም ውጤቱ በግልጽ ታውቆ የተመሰከረላቸው ነቢያት እነማን እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም ።

አዎ ሁሉንም በዚህ ጽሑፍ ለመዘርዘር ስለሚያዳግት ለመረጃ ያህል ከብዙዎቹ የጥቂቶቹን ነቢያት ትንቢት ብቻ አልፎ አልፎ መግለጽ ግዴታ ይሆንብናል ። በአሪት ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን (መዋሐድ) ፤ ወደዚህ ዓለም መምጣት፤ ስለ አዳኝነቱም የሚገልጹ የትንቢት ቃላት ይገኛሉ ። እነዚህም አንደኛ ዘፍጥረት ሦስት፤ አሥራ አምስት ስለቅንዋቱና ዲያብሎስን ስለማሠሩ ፤


፪ኛ ዘፍጥረት ፱ ፳፮ ፤ ከሴም ዘር ስለመወለዱ ፤ ፫ኛ ዘፍ ፲፪ ፫ ከአብርሃም ዘር በሚወለደው በኢየሱስ ዓለም ስለመዳኑ ፤

፬ኛ ዘፍ, ፲፯ ፯-፲፱ እግዚአብሔር ከአብርሃም ዘር ለመወለዱ ስለተነገረው ቃል ኪዳን፤ ፭ኛ ዘፍ. ፲፰ ፲፰፡ አብርሃም በሥጋ የክርስቶስ አባት ስለመሆኑ ፤

፮ኛ ዘፍ. ፳፩. ፲፪ አብርሃም ብዙ ልጆች ሲኖሩት የተስፋው ልጅ ክርስቶስ የሚወለደው በይስሐቅ ዘር ስለመሆኑ ፤ ፯ኛ ዘፍ፡ ፳፪፡ ፲፰ ከአብርሃም የዘር ሐረግ በተወለደው መሢሕ የዓለም ሕዝብ ጽድቅን ስለማግኘቱ ፤ ስምንተኛ ዘፍ፡ ፳፮፡ ፬ በአብርሃም ዘር በክርስቶስ የዓለም ሕዝብ ስለመዳኑ ፤ ፱ኛ ዘፍ ፵፱፡ ፲ ያዕቆብ አሥራ ሁለት ልጆች ሲኖሩት በተለይ የመንግሥትና የገዢነት ሥልጣን ከተሰጠው ከይሁዳ ዘር ንጉሠ ሰላም ክርስቶስ ስለመወለዱ ፤ ፲ኛ ፤ ዘፀ ፲፪ ፤ ፵፮ ከመስቀሉ ሲወርድ አፅሙ ስለ አለመሰበሩ ፤ ፲፩ኛ ፤ ዘኁልቍ ፳፬ ፤ ፲፯—፲፱ ከያዕቆብ ዘር ክርስቶስ (ኮከብ) ስለመውጣቱ ባዕድ አምልኮትን ስለማጥፋቱና የሁሉ በላይ ስለመሆኑ ፣ ፲፪ኛ ዘዳ ፲፰፡ ፲፭—፲፰ ክርስቶስ ከእስራኤል ዘር ስለመወለዱና ስለማስተማሩ ፤ ፲፫ኛ ዘዳ፤ ፴፪፡ ፵፫ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ምሕረትና ይቅርታ ስለማድረጉ ፲፬ኛ ሁለተኛ ሳሙ ፡ ፯፡ ፲፪ ፲፮ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ስለመወለዱና የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ስለመያዙ ከዳዊት ዘር የሚነሣው ሥጋ በተዋሕዶ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ስለመሆኑ ፤ ፲፭ኛ ኢዮብ ፲፱ ፡ ፳፭ ከሰማይ ወርዶ ምድራዊ ሥጋን ተዋሕዶ ዓለምን ስለማዳኑ ፤ ፲፮ መዝ ፪፡ ፩ ፡ አይሁድ እንግደለው ብለው ስለሚመክሩበት ፤ ፲፯ኛ መዝ፡ ፳፡ ፪—፯ በሆሣዕና ሕፃናት ስለሚያመሰግኑት ፤ ፲፰ኛ መዝ

www.ethiopianorthodox.org

፲፯ ፫ —፲፩ በትንሣኤው ሙስና መቃብርን (መፍረስ መበስበስን) አጥፍቶ ሕያው ሆኖ ስለመነሣቱ፤ ፲፱ኛ፤ መዝ፡ ፲፫ ፵፱ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱን አብን ስለማመስገኑ ፤ ፳ኛ መዝ፡ ፶፱፡ ፬ ስለሐዋርያት ስብከት ፤ ፳፩ኛ መዝ፡ ፳፪ ፩—፳፩ ስለክርስቶስ ጸሎትና ስለነገረ መስቀሉ ፤ ፳፪ኛ መዝ፡ ፳፯ ፲፪ አይሁድ በሐሰት አስመስክረው ስለ ሚሰቅሉት ፤ ፳፫ኛ መዝ፡ ፴፡ ፫ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሕያው ሆኖ ስለመነሣቱ ፳፬ኛ መዝ፡ ፴፩፡ ፭ ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ነፍሱን ለአባቱ አደራ ስለመስጠቱ ፤ ፳፭ኛ መዝ፡ ፴፭ ፯ ፲፭ አይሁድ በደግ ፊንታ ክፉ መክረው ለሞት እንዳደረሱት ፤ ፳፮ኛ መዝ፡ ፴፫፡ ፲፫ ክርስቶስ መከራውን የተቀበለው በትዕግሥትና በአርምሞ ስለመሆኑ ፤ ፳፯ኛ መዝ፡ ፵፡ ፮—፲ ወልድ ስለ አብ ስለራሱ ስለመንፈስ ቅዱስ ስለማስተማሩ ፤ ፳፰ኛ መዝ፡ ፵፩ ፭—፱ ፲ ፤ አይሁድ በምቀኝነት ክፉ ስለመከሩበት እንጀራውን የሚበላው ይሁዳ አሳልፎ ስለሚያሲዘው ፤ ፳፱ኛ መዝ፡ ፵፡ ፵፭ ፮—፫ ስለ ክርስቶስ መንግሥት ፤ ፴ኛ፡ መዝ፡ ፶ ፫—፯ ስለምጽአተ ክርስቶስ ፤ ስለ ፍርዱ ፤ ስለ ኅልፈተ ዓለም ፤ ፴፩ኛ መዝ፡ ፶፭፡ ፲፪—፲፭፡ ፳፫ ክርስቶስን የጠሉትና ክፉ የተናገሩት ወገኖቹ ስለመሆናቸው ፤ ፴፪ኛ መዝ ፶፯፡ ፭ ፈሪሳውያን ልዩ ልዩ ክርክርና ጥያቄ እያቀ



« ከአብራክህ ፍሬ በዙፋንህ አስቀምጣለሁ »



ረቡ በክፉ ወጥመድ ሊያጠምዱት ስለመጣራቸው ፤ ፴፫ኛ መዝ፡ ፷፫ ፬፡—፲፪ (፳) ፳፩ ክርስቶስ ሰይጣናትን ስለመቀጥቀጡ ፤፴፬ኛ መዝ፡ ፷፱ኛ ፬—፱ (፳) ፳፩ አይሁድ በከንቱ ስለጠሉትና ተጠማሁ ባለ ጊዜ ሐሞት እንዳጠጡት ፤ ፴፭ኛ መዝ፡ ፸፪ ፫—፲ ስለክርስቶስ መንግሥት ፤ በተወለደም ጊዜ ሰብአ ሰገል እንደሰገዱለት ፤ ፴፮ኛ መዝ፡ ፸፰ ፪ ስለ ክርስቶስ ትምህርት ፤ ፴፯ኛ መዝ፡ ፹፱ (፳) ፳፮ (፳፯) ፵፭ ወልድ አባቴ ብሎ ስለ አብ ስለ ማስተማሩ ፤ አብም የባሕርይ ልጄ ነው ብሎ ስለ ወልድ ስለ መመስከሩ ፤ ፴፰ኛ መዝ፡ ፩፻፪ ፳፬ ፳፯ ስለ ሕልፈተ ዓለም ፤

፴፱ኛ፡ መዝ፡ ፩፻፱፡ ፬ በወደዳቸው ፋንታ አይሁድ ስለሚጠሉት ፤ ፵ኛ፡ መዝ፡ ፩፻፲ ፩—፬ ስለ ክርስቶስ ዕርገትና ሊቀ ክህናት ስለመሆኑ ፤ ፵፩ኛ፡ መዝ፡ ፩፻፲፰ ፤ ፳፪—፳፯ አይሁድ እሩቅ ብእሲ ነው ብለው ቢገድሉት የባሕርይ አምላክ ሆኖ ስለመነሣቱ፤ ፵፪ኛ፡ መዝ፡ ፩፻፴፪፡ ፲፩ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ተወልዶ ዙፋኑን ስለ መውረሱ ፤ ፵፫ኛ፡ ምሳሌ ፰፡ ፳፪—፴፭ ከዓለም በፊት እንደተወለደና በኋለኛውም ዘመን በትምህርቱ ሰዎችን ስለማቅረቡ ፤ ስለ ርደቱና ስለዕርገቱ ስለስሙና ስለአባቱ ስም፤ ፵፬ኛ፡ ኢሳ፡ ፪ (፪) ፫ ስለ ሕገ ወንጌል ፤ ስለ ክርስቶስ ማስተማር ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን ፤ ፵፭ኛ፡ ኢሳ፡ ፯፡ ፲፬ ከድንግል ስለመወለዱ ፤ ስሙ አማኑኤል ስለመባሉ ።

፵፮ኛ ኢሳ፡ ፰፡ ፲፬ ለማያምኑት ለቤተ እስራኤል የመሰናከያ ድንጋይ ስለመሆኑ። ፵፯ኛ| ኢሳ፡፱፡ ፩፡ ፪፡ ፮—፯ በኃጢአት ጨለማ የሚኖረው ሕዝብ በክርስቶስ ብርሃን ስለማግኘቱ ፤ ስለልደቱ ፤ ስለመንግሥቱ፤ ፵፰ኛ | ኢሳ ፲፩ ፩ ፲ ከዕሤይ ዘር ከተገኘች ከድንግል ማርያም ስለመወለዱ ፤ ፵፱ኛ| ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፱ ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ በግልጽ ስለመታየቱ ፤ ፶ኛ ኢሳ ፳፰ ፡ ፲፮ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ደንጊያ ስለመሆኑ ፤ ፶፩ኛ ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፲፫ ፈሪሳውያን በአፍ እየደለሉ ለክፉ ስለሚያስቡት ፶፪ኛ | ኢሳ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ስለ ክርስቶስ መንግሥትና ግዛት ፶፫ኛ | ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፬—፯ ስለ ሰማይና ምድር ማለፍ፤ ፶፬ኛ | ኢሳ ፡ ፵ ፡፫—፲ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ አዋጅ ነጋሪነት ፤ ስለ ክርስቶስ መገለጥ ፶፭ኛ |ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፩ — ፬ ፡፯ ፡ ፯ ስለ ክርስቶስ ትምህርት ልዝብነትና ትዕግሥት ፤በትምህርትና በተአምራቱ ዓለምን ስለማዳኑ ፤ ፶፮ኛ፡ ኢሳ ፡ ፵፭፡ ፳፫ ስለ እግዚአብሔር አምልኮት በግልጽ መታወቅ ፤ ፶፯ኛ፡ ኢሳ፡ ፵፱፡ ፩ - ፯ ስለክርስቶስ ትምህርትና አዳኝነት ፤ ፶፰ኛ፡ ኢሳ፡ ፶፡ ፯ ስለመገረፉ ፤ በጥፊ ስለ መመታቱ ፤ በምራቅ ስለሚተፉበት ፤ ፶፱ኛ፡ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፩፡ ፬—፱—፲፪ ስለ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል ፤ ፷ኛ፡ ኢሳ፡ ፶፬፡ ፲፫ ስለ ክርስቶስ ማስተማር ፤ ፷፩ኛ፡ ኢሳ፡ ፶፭ በሙሉ፤ ስለ ሥጋውና ደሙ ስለ ትምህርቱ ፤ ፷፪ኛ፡ ኢሳ፡ ፶፱፡ ፳ ስለ መድኃኒታችን መምጣት ፤ ፷፫ኛ፡ ኢሳ፡ ፷፡ ፫—፯ ስለ ቤተ ክርስቲያን ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያት ስለ ሰብአ ሰገል በግመል ወርቅ ማምጣት ፤ ፷፬ኛ፡ ኢሳ፡ ፷፩፡ ፩፡ ስለ ክርስቶስ አዳኝነትና ትምህርት፡ ፷፭ኛ ኢሳ፡ ፷፪ ፲፩ ስለ መድኃኒት መምጣት ፤ ፷፮ኛ፡ ኢሳ፡ ፷፫፡ ፫፡ ክርስቶስ በመስቀሉ ሰይጣናትን ስለመቀጥቀጡ ሰዎችን ስለማዳኑ ፤

፷፯ኛ፡ ኢሳ ፷፭፡ ፪ ክርስቶስ በጸጋው ዓለምን ስለማዳኑ ። ፷፰ኛ፡ ኤር፡ ፳፫፡ ፩—፰ ስለ እረኞቹ መምህራንና ስለ በጐቹ ምእመናን ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፱ኛ፡ ኤር፡ ፴፩፡ ፲፭| ፳፪፡ ፴፩—፴ ስለ ቤተ ልሔም ሕፃናት ማለቅ ፤ ስለ ሐዲስ ኪዳን መሰጠት ዓለም በክርስቶስ ስለማመኑ ፤

፴ኛ፡ ኤር፡ ፴፫፡ ፲፬—፳፮ ስለ ሐዲስ ኪዳን ስለ ክርስቶስ ንጉሥነትና ሊቀ ካህናትነት መሥዋዕት ሆኖ ዓለምን ስለማዳኑ ፤ ፴፩ኛ፡ ሕዝ፡ ፴፬፡ ፳፫፡ ፳፬ ክርስቶስ አውሬዉን ዲያብሎስን ገድሎ መንጋዉን ምእመናንን ስለመጠበቁ ፤

፴፪ኛ፡ ዳን፡ ፪፡ ፴፬ ስለክርስቶስ ዘለዓለማዊ መንግሥት ፤ ፴፫ኛ፡ ዳን፡ ፱፡ ፳፬፡ ፳፯ ስለ ክርስቶስ መምጣትና ስለ ኃጢአት መደምሰስ ፤ ፴፬ኛ፡ ሆሴ፡ ፮፡ ፪ ክርስቶስ በሞቱ እኛን ስለማዳኑና በሦስተኛው ቀን ፈራሽ በስባሽ ሥጋችንን ስለማስነሳቱ ፤ ፴፭ኛ፡ ሆሴ፡ ፲፩ ፡ ፩ ኢየሱስ ወደግብፅ ተሰዶ ከስደት ሀገሩ ስለመመለሱ ፤

፴፮ኛ፡ ኢዮ፡ ፪፡ ፴፪ ዓለምአባታችን ሆይ ብሎ የእግዚአብሔርን ስም በጸሎት ጠርቶ ለመዳን ዕድል ስለማግኘቱ ፤ ፴፯ኛ፡ አሞ፡ ፭፡ ፳ ስለ እግዚአብሔር ቀን (ስለ ዘመነ ሐዲስ) ። ፴፰ኛ፡ ሚክ፡ ፬፡ ፩ ስለጽዮን ስለ ቤተ ክርስቲያን ስለ መንግሥተ ሰማያት ፤ ፴፱ኛ፡ ሚክ፡ ፭፡ ፩—፫ ክርስቶስ በኤፍራታ ግዛት በቤተ ልሔም ስለ መወለዱ ጉንጩን በጥፊ ሰለመመታቱ ፤ ፵ኛ፡ ሐጌ፡ ፪፡ ፯፡ ፱ ስለ ቤተ ክርስቲያን ፤ ቤተ ክርስቲያንም ከአሪቱ መቅደስ ስለመብለጧ ፤

፵፩ኛ፡ ዘካ፡ ፫፡ ፰ በክርስቶስ ስለሚደረገው የኃጢአት ሥርየት ፤ ፵፪ኛ፡ ዘካ፡ ፮፡ ፲፫ ቤተ ክርስቲያንን ስለመመሥረቱ ፤ ንጉሥና ሊቀ ካህናት ሆኖ ለዓለም ሰላም ስለማምጣቱ ፤ ፵፫ኛ፡ ዘካ፡ ፱፡ ፱ በሆሣዕና በአህያ ላይ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም ስለ መግባቱ ፤ ፵፬ኛ፡ ዘካ፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፲፫ ክርስቶስ በ፴ ብር ስለ መሸጡና ገንዘቡም ለሸክላ ሠራተኛ ስለመዋሉ ፤ ፵፭ኛ፡ ዘካ፡፲፪ ፲ በጦር የወጉትን በጸጋው አቅርቦ ስለማዳኑ እሱን ለማምለክ ስለማብቃቱ ፤

፵፮ኛ፡ ዘካ፡ ፲፫፡ ፯፡ ፯ እጁን በምስማር ቸንክረው ስለማቊሰላቸው እረኛዉን ክርስቶስን ገድለው በጎቹን ለመበተን ስለማሰባቸው ፤ ፵፯ኛ፡ ዘካ፡ ፲፬፡ ፬፡ ፰ ስለ ምጽአተ ክርስቶስ፤ ፵፰ኛ፡ ሚልክ ፡ ፫፡ ፩ መጥምቁ ዮሐንስ ከክርስቶስ ቀድሞ ስለ ማስተማሩና መንገዱን ስለመጥረጉ ፤

፵፱ኛ፡ ሚልክ፡ ፬፡ ፭ ዮሐንስ ኤልያስ በሚል ስያሜ ተሰይሞ ቀድሞ መጥቶ የንስሓ ትምህርትና ጥምቀት ስለማድረጉ ፤ እነዚህን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና እነዚህንም የመሳሰሉትን የትንቢት ቃላት ራሱ ክርስቶስ በወንጌሉ ፤ ሐዋርያትም በመልእክቶቻቸው ገልጸዋቸዋል ። ለመረጃም ያህል ባጭሩ ማቴ፡ ፩፡ ፳፪—፳፬ ። ፪፡ ፭ ። ሉቃ፡ ፳፬፡ ፳፭—፳፯ ።
ዮሐ፡ ፩፤ ፩—፲፰ ። ፭፡ ፬፡ ፲፱ ። ማር፡ ፩፡ ፩—፬ ። የሐ፡ ሥ፡ ፩፡ ፲፭—፳፩ ። ፪፡ ፲፬—፳፩ ። ፰ ፡ ፴፪—፴፬ መመልከትና ሌሎችንም በዚሁ ማስተዋል ይቻላል ። ስለ ዚህ በመካከለኛው ዘመን የሕዝብን ኃጢአት ለማስወገድና የመንፈስ ነፃነትን ሰላምንም ለመመሥረት የመሢሕ (የክርስቶስ) መምጣት ይህን በመሳሰለው ግልጽና ትክክለኛ እውነትን የተመረከዙ የትንቢት ቃላቶች ከተነገሩና ለንስሐ የመዘጋጃው ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ መሆኑን መዘንጋት የለብንም ።

መክብብ አጥናው ።



## ም ዕ ራ ፍ ፪ ።

## በክርስቶስ ልደት ታላቅ የምሥራች ።

ትንቢተ ነቢያት ተተረጐመ ጉልቄ ሱባኤ ተፈጸመ ።

በርእሰ ነገሩ እንደተገለጸው ይህ ታላቅ የምሥራች ከዚያ በፊት ተደርጎ አያውቅም ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም እገሌ ከእገሌ ሳይባል ለመላው ዓለም ከአዳም ተወለደ ለሰው ልጅ ሕይወት ሰላም ብርሃን የሚያድልና ቤዛ የሚሆን መድኅን ተወለደ ።

እውነተኛ ፍትሕ ትክክለኛ ሚዛን ፤ ፍጹም ነፃነት የሚሰጥ ንጉሥ እነሆ ወደ ዓለም መጣ ፀብ ክርክርን የሚያርቅ ፤ ድንቁርናን የሚደመስስ ዕውቀት ፤ ጥበብ ኃይል ብርታት ፤ ለሰው ልጅ ሁሉ የሚያድል እውነተኛ መምህር ዛሬ ተገለጠ ።

ዕውራኖችን የሚያበራ ፤
ጐባጦችን የሚያቀና ፤
አንካሶችን የሚያረካ ፤
ለምፃሞችን የሚያነፃ ፤
የታረዙትን የሚያለብስ ፤

የተራቡትን የሚያጠግብ ፤ ተየጠሙትን የሚያረካ ፤ የወደቁትን የሚያነሣ የታመሙትን የሚፈውስ ፤ እውነተኛ ዶክተር ፤ ዮም ተወልደ ዛሬ ተወለደ እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደሰማነው ይህን የመሰለ ታላቅ የምሥራች በዓለም ላይ ከአሁን ቀደም ማለት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንዳልተነገረና ከእንግዲህም ወዲህ ይህንኑ መላልሰን ከማድነቅ በቀር ሌላ አዲስ የምሥራች እንደማይነገር እያንያንዱ ምእመን በታሪካዊና ትንቢታዊ ዓይኖቹ አንብቦ ለመረዳት መብት አለው ።

ይህም ማለት አምላክ ክርስቶስ ሁለተኛ በሥጋ አይወለድም ማለት ነው ፤ የሌሎች ልደት እንደ ጌታ ልደት ታላቅ የምሥራች ነው አያሰኝም ከአሁን ቀደም የነበሩ ዛሬም ያሉ ከእንግዲህ ወዲህም የሚነሡ የዓለም ታላላቅ ሰዎች የሰጡትም ሆነ የሚሰጡት ታላቅ አገልግሎት የሚፈጽሙትም ታላቅ ግዳጅ ለተመረጡበት ፤ ለተወለዱበት በጠቅላላው ዜጋ ሆነው ለሚኖሩበት አገር ብቻ እንጅ ለጠቅላላ ዓለም ደማቸውን አፍሰው ፤ አጥንታቸውን ከስክሰው ፤ እንደ ጌታ የዘለዓለም ሕይወትና ፍጹም ነፃነት የሚሰጡበት ጊዜ የለም ። ይኸውም ከሞላ ጐደል ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰማያዊ ፤ ቀዳማዊ የማይሞት ኃያል፤ የማይታይ ረቂቅ ዓለምን በቃልነቱ የፈጠረ ፈጣሪ ሲሆን ስለ ዓለም ሕይወት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፤ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን እንደአዳነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምረናል።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህም ነቢያት ፣ ነገሥታት ካህናት ፣ ሌሎችም ሊቃውንት በሰማይና በመሬት ምሉዕ ሆኖ የሚኖር ሥነ ፍጥረት በሙሉ ሳይለያይ በመተባበር እንደ አንድ ልብ መክረ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ቤዛ ኵሉ ዓለም ዮም ተወልደ በማለት ይዘ ምራሉ ያመሰግናሉ ይህም ማለት የዓለም ቤዛ መድኃኔ ዓለም ዛሬ ተወለደ ማለት ነው ።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ አለ ፤ ጥያቄውም ከዓለም ታላላቅ ሰዎች ውስጥ የዓለም ቤዛ የተባለ አለን ? የሚል ሲሆን መልሱ በፍጹም የለም ነው ። ከላይ እንደገለጽ ነው ከሞላ ጐደል ሁሉም ለሆነባት አገር ብቻ ካልሆነ በስተቀር የዓለም ቤዛ የሆነ አልነበረም ፤ አይኖርም መድኃኒታችን ኢየሱስ ግን በ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ሌሊት በቤተ ልሔም ዋሻ በነበረው የከብቶችና ያህዮች በረት ውስጥ ከእ መቤታችን ተወለደ ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም እንደተወለደ ።



አህዮችና ከብቶች ፈጣሪያቸው መሆኑን ተረድተው ጊዜው ብርዳማና ውርጫማ ስለነበር እስትንፋሳቸውን በመገበር አሟሟቁት። ከዚህ ላይ አንድ አስደናቂ የሆነ ምሥጢር አለ ይኸውም ከብቶችና አህዮች ሳይማሩ አስተማሪዎች ሳይቀጠሩላቸው ሕግ ሳይሠራላቸው መጻሕፍት ሳይጻፉላቸው ትምህርት ቤት ሳይሠራላቸው በተፈጥሮ ጠባያቸው አውቀውና ተረድተው ለአምላካቸው የእስትንፋስ ግብር መገበራቸው ነው ።

በዚያን ሰዓት መጻሕፍተ ብሉያትን እንተረጕማለን ኃላፍያትንና መጻእያትን እናውቃለን የሚሉ ምሁራን በኢየሩሳሌም ተኝተው ነበር ፤ የጌታ ልደት በገሀድ ቀርቶ በሕልም እንኳን አልተገለጸላቸውም ሌላ ሕልምና ቅዠት ነበር ሲያዩት ያደሩት ፤ በጌታ ልደት ለብዙ ዘመናት ተለያይተው የነበሩት ማኅበረ መላእክትና ደቂቀ አዳም በአንድነት ሆነው ስብሓት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ፤ ለእግዚአብሔር በሰማይ ምስጋና ይሁን በምድርም ሰላም በማለት ዘመሩ በጠፈር የነበረው የአጥቢያ ኮከብ ወደ መሬት ዝቅ በማለት ወደ ክርስቶስ የሚያመሩትን የሳባንና የዓረብን ነገሥታት መርቶ በቤተ ልሔም ዋሻ ክርስቶስና እናቱ ወደ ነበሩበት አደረሳቸው ፤ ማቴዎስ ም| ፪ ቍ| ፩ እስከ መጨረሻው ተመልከት ።



ሰብአ ሰገል በኮከብ መሪነት መጥተው እንደገበሩለት ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰብአ ሰገል በኮከብ እየተመሩ ብዙ መንገድ ተጉዘው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አስፈላጊዎች የሆኑትን በጊዜው የተወደዱ ገንዘቦችን ገበሩለት።የግብሮቹምዓይነቶች፤

፩ኛ| ወርቅ ፡ ንጉሠ ባሕርይነቱን ሲተረጉሙ ፤

፪ኛ| ዕጣን ፤ መዓዛ ቅዱሳን ነህ ሲሉ ፤

፫ኛ| ከርቤ ፤ ስለ ዓለም ትሞታለህ በማለት ገበሩለት ፤ የሰማይ መላእክትና የምድር እረኞች ምስጋና ሲገብሩለት ፡ ከብቶችና አህዮችም እስትንፋሳቸውን ገበሩለት ብለናል ይህ ሁሉ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ የተወለደው በከብቶች በረት ነበር ፤ እናቱ ማርያም ሌላ ልብስና ምንጣፍ ስላጣች ቅጠል ቆርጣ አነጠፈችለት ፤ ቅጠልም ጋረደችለት በዓለም ላይ የነበሩ ወንዞች ውቅያኖሶች ጣዕማቸው ወደ ማርና ወተት ተለውጠው በደስታ እንደዋሉ ብዙ ደራስያን ያስረዳሉ ። በተለይም ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ብዙ ሰላም ፤ ብዙ ሕይወት ፤ ብዙ ተአምራት እንደተደረገ ድጓ በተባለ ድርሰቱ በሰፊው ያስረዳል። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ፍጹም ሕይወት ታላቅ ሰላም የመሠረተ መሆኑን በመረዳት ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ማክበር እንደሚገባው በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠ ነው ። ፍሥሐ ጽዮን ክሣዬ

## ም ዕ ራ ፍ ፫ ።

### ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም ።

### የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሰሙነ ልደት ከምትዘምራቸው መዝሙሮች በይበልጥ ሰፋ ያለውን ቦታ ይዞት የሚገኘው «ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ» የሚለውና የመሳሰለው ዓረፍተ ነገር ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የጌታችን ክርስቶስን ልደት በምታከብርበት ዕለት ከቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢርና ምሳሌ ተወራርሶ ሲያያዝ በመጣው በመልክም ባሕልና ሥርዓት ታከብረዋለች ።

ይህ በዓል እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ከማታው እስከ መንፈቀ ሌሊት ጣዕም ባለው ዝማሬና ማኅሌት ሲከበር ከቈየ በኋላ አስደናቂነት ያለው ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ለልደት ያዘጋጀችው ባሕል ይታያል ።

፩ኛ. መዘምራኑ «በጎል ሰከበ» የሚለውን ዕዝል መርተው ከጻፉ በኋላ "ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም፡— የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ «የሚለውን ምልጣን በሚያስደንቅ አኳኋን በማሸብሸብ የምሥራቹን ያበሥራሉ ፤ በኋላም ስብሓተ ነግህ አድርሰው ሲፈጽሙና ከሰላም ሲደርሱ ተሰልፈው ወደ ቤተ ልሔም ይወርዱና «ንሰብክ ወልደ የሚለውን ሰላም መርተው በመሶበ ወርቅ ያለውን ኅብስቱን ፤ በጽዋዕ ያለውን ወይኑን ከቤተ ልሔም አጅበው « መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ የሀበነ



ሰላመ ጋዳ ያበውዕ ቍርባነ ፡ ዓለምን ሊያድን ፤ ሰላምን ሊሰጠን መጣ ሰብአ ሰገልም እጅመንሻውን ቍርባን አገቡ» የሚለውን ምልጣን እየዘመሩ በምሥራቅ ገብተው በሰሜናዊ በር ዞረው በቅኔ ማኅሌት በኩል በዓምደ ወርቅ ያገቡታል ። ይህም ባህልና ሥርዓት ብዙ ምሳሌና ትርጉም አለው ።

ሀ. በኦሪት እሥራኤል ከግብፅ ከወጡ በኋላ መና እየዘነመላቸው ይመገቡ ስለነበር ከመናው ለትውልድ ተላልፎ ለምስክር ይቀመጥ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎታል» ከመናው አንድ ጎሜር ሙሉ ፤ ከምስር ባወጣኋችሁ ጊዜ በምድረ በዳ ያበላሁዋችሁን ልጆቻችሁ ያዩ ዘንድ ለሚመጣው ትውልድ ይቀመጥ ።

ጎሜር የዕብራውያን የደረቅ ነገር መስፈሪያ ነው ፤ ልኩ ገበርሾ ያህላል ሙሴም ትእዛዙን ከተቀበለ በኋላ ካህኑን አሮንን እንዲህ አለው « ማድጋ ውሰድና መና ጨምርበት አንድ ጎሜር ያህል አግባበት ለትውልድም ይተላለፍ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት አስቀምጠው» አሮንም በምስክሩ ድንኳን በጎሞር አስቀመጠው በዚህ መሠረት እስራኤል በሚዘዋወሩበት ሁሉ ይህን በጎሞር ያለ መና አብረው ይዘውት ይዞሩ ነበር ፤ ኦሪት ዘፀአት ፲፯. ፴፪-፴፭ ።

ይህ ጎሞረ መና እስከ ልደት ቈይቶ ያንለት ጠፋ ይባላል ፤ በልተውት የሚርበው መና ጠፋ ፤ በልተውት የማይርበው እውነተኛው ኅብስተ ሕይወት ተተካ ሲሉ በዚህ ምሳሌ ነው መሶበ ወርቁን አጅበው ዞረው የሚገቡት፣ ይባላል ።

ለ| ወደ ቤተ ልሔም ወርደው ዓለምን ሊያድን ለኛም ሰላምን ሊሰጠን መጣ እያሉ እያሸበሸቡ የሚመለሱት ደግሞ መላእክት ከሰማይ ወርደው በቤተ ልሔም ሕፃኑን «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ፡ ለእግዚአብሔር በሰማያት ምሥጋና ይገባል ለሰውም እንደ ፍላጎቱ በምድርም ዕርቅ ሆነለት» ብለው እያመሰገኑ ወደ አርያም ለማረጋቸውና እረኞችም መልአኩ «እስመ ናሁ ተወልደ ለክሙ ዮም መድኅን ዘውእቱ ክርስቶስ እነሆ ዛሬ መድኅን ተወልዶላችኋል እሱም ክርስቶስ ነው» ብሎ የምሥራቹን በነገራቸው መሠረት «ኑ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድና ይህን እግዚአብሔር የገለጠልንን ነገር እንረዳ» ብለው መንጎቻቸውን በዱር ትተው ወደ ቤተ ልሔም ሄደው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አግኝተውት ተደንቀው እያመሰገኑ ለመመለሳቸው ምሳሌ ነው ። ሉቃስ ፪፥ ፰—፳ ።

ሐ| በጠቅላላው የመዝሙሩ አነጋገር እንደሚያመለክተው «ሰላምየ እሁበክሙ ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ» ብሎ ለዓለም ሰላምን የሚያድል፥ ዓለምን በደሙ የሚያድን እውነተኛ ኅብስተ ሕይወትና ጽዋዐ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም ተገኘ ወይም ተወለደ ለማለት ነው ።

መ| መሶበ ወርቁ እንደ ተለመደው በምሥራቅ ኆኅተ መቅደስ ሳይሆን በዓምደ ወርቅ በር የሚገባበት ምክንያት የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት እንደሚናገሩት ገነት እንደ ምሥራቅ ፤ ሲዖል እንደ ምዕራብ ስለሚቈጠሩ አዳምን ከጨለማ ቦታ ከሲዖል ለማውጣቱ ምሳሌ ነው ይባላል ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ኛ] በቤተ ክርስቲያናችን ባሕልና ሥርዓት በበዓለ ልደት እንደ ጥምቀት ፤ እንደ ትንሣኤ ፤ በመንፈቀ ሌሊት ነው የሚቀደሰው ፤ ይህም ጌታ የተወለደው ሌሊት ስለ ነበር የዚያ ምሳሌ ነው ፤ ይኸውም ወንጌሉ «ወሀለዉ ኖሎት ውስተ ውእቱ ብሔር ወይትጌሁ ወይሔልዉ ወየዐቅቡ መራዕዪሆሙ ሌሊተ ፡ በዚያም ሀገር ሌሊት መንጋ ቸውን ነቅተው ተግተው የሚጠብቁና የሚያግዱ እረኞች ነበሩ» ባለው መሠ ረት ፤ የጌታን መወለድ ከመልአኩ ቃል ሰምተው የምሥራቹን ለማየት መንጎቻቸውን ጥለው የሄዱት የሌሊት እረኞች ነበሩ ፤ በዚህ ሊታወቅ ይቻላል ። (ሉቃስ ፱፡ ፰)

፲ኛ] ጸሎተ ቅዳሴውና ዕጣነ ሞገሩ ከተፈጸመ በኋላ ልዑካኑ (ቀዳስያኑ) ልብሰ ተክ ህኖዋቸውን እንደ ለበሱ መዘምራኑም ከበሮና ጸናጽላቸውን እንደ ያዙ ወደ ውጭ ወደ ዓውደ ምሕረት ይወጡና ገባሬ ሠናይ የሆነው ቄስ «ወተመይጡ» የሚለውን ምዕዋድ መርቶ እሩሩን ለግቶ ለመዘምራኑ ይሰጣል ። መዘምራኑም እየተቀባበሉ ይመ ቱና ለሕዝቡ አቀብለው «ወተመይጡ ኖሎት እንዘ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ፡ እረ ኞቹ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ተመለሱ» የሚለውን የምዕዋዱን ምልጣን እያሸበ ሸቡ ዘረው ይመለሳሉ ።

በሀገራችንም ነገሥታቱ ሩሩዋን ለግተው ለመኳንንቱና ለወታደሮቻቸው ያቀብ ላሉ ፤ ሕዝቡም በልደት ዕለትና በሰሞኑ በየ ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ በሚገኘው አድ ባርና በማርገጃው ሩሩን (ጥንጉን) እየተቀባበሉ ይመታሉ ፤ ሩሩንም በበዓሉ ስም ገና ይሉታል ። ገና ማለት በግሪክ ቋንቋልደት ማለት ነው ፤ ይህም ጌናዎ (ጌኖ) ወለደ ከሚ ለው ግሥ የወጣ ነው ፡ ሩር ፤ (ጥንግ) ከእሥራኤል ሲያያዝ የመጣ ባሕል ነው ፤ እሥ ራኤል በዓመት በዓል ሩር ይመቱ ነበር ይባላል ሩር ጨዋታ በእሥራኤል እንዳለ ለመ ረዳት ቀላል ነው ፤ ንጉሣቸው ዳዊት ከመ ኳሄላ ክንክዎሙ ለብዙኃን ለብዙዎቹ እንደ ሩር መጫዋቻ ሆንሁዋቸው» ብሎ በመዝሙሩ ተናግሯል መዝሙር ፷፡፺ ።

ግን በተለይ በገና ዕለት ቄሱ ወተመይጡን መርቶ ሩሩን ለግቶ ለመዘምራኑና ለሕዝቡ ሰጥቶ ካህናቱ ሩሩን ከመቱ በኋላ እረኞቹ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ተመለሱ» የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር እየዘመሩ የመመለሳቸው ዋናው ምሳሌና ትርጉም የመዝሙሩ ምሥጢር እንደሚያስረዳው መድኃኒታችን በተወለደ ዕለት የቤተ ልሔም እረኞች ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አይተው በመደነቃቸው ከእሥራኤል ሲያያዝ በመጣው ልማድ ተደስተው ሩር እየተቀባበሉና እግዚአብሔርን እያመ ሰገኑ ለመመለሳቸው ምሳሌ ነው ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን በአባቶቻችን አማካይነት መሠረትና ታሪክ ያለ ውን ባሕል ጠብቃ ስለአቈየችን ልንደሰትበትና ልንኰራባት ይገባል ፡ እኛም ይህን ከመሰለው አስደሳችና አገርን ከሚያኰራ ታሪካዊ ባሕል ሳንቀንስ ጠብቀን ለትው ልድ ማስተላለፍ ይኖርብናል ።

ክንፈ ገብርኤል አልታዩ



## ም ዕ ራ ፍ ፩

## በበሕቅ ልሕቀ (ጥቂት በጥቂት አደገ )

የተነገረው ትንቢት የተቈጠረው ሱባዔ ሲፈጸም የእሥራኤል ተስፋ የዓለም መድኅን ክርስቶስ ያለአባት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ።

አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ይህ በፍጡር ዘንድ ሲታሰብ ዕፁብ ነው ድንቅ ነው በፈጣሪ ዘንድ ግን ቀላል ነው ። ዓለምን ለማዳን ሰው የሆነው አምላክ በጨርቅ ተጠቀለለ በከብቶችም በረት አደረ በዚያን ጊዜ ከመላእክትና ከእ ንስሳት በስተቀር ያየው አንድም አልነበረም ። በዚያን ጊዜ በንጉሡ በአውግስጦስ ቄሳር አዋጅ መሠረት በቤተልሔም አውራጃ ይጻፍ ዘንድ የተሰበሰበው ሕዝብ እጅግ የበዛ ነበር ። ነገር ግን የሕፃኑ የክርስቶስ በበረት መወለድን ለመስማትና ለማ የት እድል ፋንታ ያገኙት የመንጋ ጠባቂዎች እረኞች ብቻ ናቸው ። የመድኅኑንም መወለድ ለማየት በቀዳሚነት ዕድል ያገኙት እረኞች ገና በኃጢአት ያልተመረዙ ንጹሐን መሆናቸው ግልጥ ነው ።

የዓለም መድኅን ክርስቶስም እንደ አምላክነቱ ፅለቱን ተወልጄ ዕለቱን ልደግ ሳይል ግዕዘ ሕፃናትን ይፈጽም ጀመረ ይህም ማለት ቀስ በቀስ አደገ ሕፃናትም በአስተዳደጋቸው ወቅት ሊያደርጉ የሚገባውን ተግባር ከዚህ ፤ እንደሚከተለው ይፈ ጽም ጀመረ ።

በዚያን ጊዜ እንደኦሪቱ ሕግ አንድ ሕፃን ሲወለድ በስምንተኛው ቀን ይገ ዘር ዘንድ በሙሴ ሕግና ሥርዓት የታዘዘ ነበር ፤ ስለዚህ በዚሁ ልማድ እናቱ ማርያ ምና አሳዳጊው ዮሴፍ ሕፃኑ ክርስቶስ እንዲገዘር ወደቤተ ግዝረት ይዘውት ሄዱ። ክርስቶስም አምላክ እንደመሆኑ በመለኮታዊ ጥበቡ የሰው ዕጅ የተጠበበበት ምላጭ ሳይነ ካው የተገረዘ ሆኖ ተገኘ ። ይህም ዕፁብ ነው ድንቅ ነው ። የሰው ሥራ ሳይሆን አምላ ካዊ ጥበብ በመሆኑ የክርስቶስ አምላክነት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተገለጠ ። በዚያን ጊዜ የነበረው ግዝረት ለዛሬዪቱ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ እናገኘዋለን፡ ዛሬ በክርስቶስ ያላመነ ያልተጠመቀ ከክርስቲያን ወገን የተለየ እንደሆነ በዚያን ጊዜም ያልተገረዘ እንደ ኦሪቱ ሕግ ከአይሁድ ወገን የተለየ ነበር ።

ሁለተኛም በሙሴ ሕግ እንደተጻፈው አንድ ሕፃን በተወለደ በአርባው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ስለአለበት እናቱ ማርያምና ዮሴፍ በአርባ ቀኑ ሁለት የርግብ ግልገልና ዋልያ ከሕፃኑ ጋር ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ ፤ በኢየሩሳሌም የሚኖር ስሙ ስምዖን የሚባል ጻድቅና የዋህ ሰው ነበር እርሱም መሢሕ ክርስቶስን ሳያይ እንዳይሞት በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ነበር እርሱም ሕፃኑ ክርስቶስን በክንዱ ታቅፎ እግዚአብሔርን አመሰገነው አቤቱ እንደቃልህ ዛሬ በሰላም አገልጋይህን ታሰ ናብታለህ ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና ለቤተ ዘመዶቼም አላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ሕፃን ከእሥራኤል ወገን ላመኑበት ሕዝብ መድኀን ፤ ላላመኑበት ግን አጥፊአ



ክርስቶስ በ፵ ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ እንደገባና አረጋዊው ስምዖን እንደታቀፈው

ቸው ነው ብሏል ።ሥነ ሥርዓቱምእንደተፈጸመ እናቱና ዮሴፍ ሕፃኑን ይዘው ወደ ገሊላ ወደከተማቸው ተመለሱ ።



፫ኛ ሁለት ዓመት ያህል ሲሆነውም ሄሮድስ በጠላትነት ስለተነሣበት ፤ ወደ ግብፅ ተሰደደ



ጌታ በሕፃንነቱ ታዝሎ ወደ ግብፅ እንደ ተሰደደ

ሕፃኑ ክርስቶስም ቀስ በቀስ አደገ ፤ ጥበብም ተመልቶበት ነበር ።

፬ኛ| የፋሲካን በዓል ለማክበር ቤተ ዘመዶቹ ወደኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር ፤ በዚሁ ልማድ ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ ከናቱና ከዮሴፍ ጋር ለበዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ ፤ የበዓሉም ወራት በተፈጸመ ጊዜ ወደ አገራቸው ተመለሱ ፤ ሕፃኑ ክርስቶስ ግን ከቤተ ዘመዶቹ ጠፍቶ በኢየሩሳሌም ቀረ ፤ እናቱና ዮሴፍም ከዘመዶቻቸው ጋር የሔዱ መስሎአቸው መቅረቱን አላወቁም ነበር ። የአንድ ቀን መንገድ [illegible] ሕፃኑንም ቢፈልጉት ሳያገኙት ቀሩ ፤ ባላገኙትም ጊዜ፡

ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ፤ ከሦስት ቀንም በኋላ በቤተ መቅደስ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውና ሲጠይቃቸው አገኙት፤ ከማስተዋሉና ከመልሱም የተነሣ ያዩት ሁሉ ያደንቁት ነበር ፤ ማርያም «ልጄ ሆይ ለምን እንዲህ አደረግኸን? እኔና ዮሴፍ ተጨንቀን እንፈልግሃለን» አለችው እርሱም መልሶ ለምን ፈለጋችሁኝ አባቴ በሚኖርበት ሁሉ መኖር እንደሚገባኝ አታውቁምን ? አላቸው ።

እነርሳቸውም ያላቸውን አስተዋሉ እጅግም አደነቁት ወደሀገራቸውም አንድ ላይ ተመለሱ፤ወደ ናዝሬትም መጡ፤ለነርሳቸውም ይታዘዝ ነበር ኢየሱስም በጥበብ በቁመት አደገ ። ሉቃስ ም፥ ፪ ቀ፥ ፵፪ —፶፪ ክርስቶስ ከሕፃንነት ጀምሮ የመጣበትን ዓላማ እስኪፈጽም ድረስ ብዙ ሥራ ሠርቷል እያንዳንዱን ዘርዝሮ ለማስረዳት ግን በሰው አንደበት ቀርቶ በመላእክት ስንኳ ያማይቻል ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ለማዳን በለበሰው ሥጋ ከኃጢአት በስተቀር ሰው ሊሠራ የሚገባውን ሁሉ በጥንቃቄ ፈጸመ ይህም ማለት አምላክ ነኝ ሳይል ቀስ በቀስ አደገ ፥ የርሱም መታዘዝ ለኛ ምሳሌና ትምህርት ሆነን ።

ሥጋን የተዋሐደው አምላክ በሰውነቱ ይፈጽም የነበረው ተግባር የመጣበትን ዓላማ ሊያሰናክልበት አልቻለም ምክንያቱም ሥጋን ከተዋሐደ በኋላ ሥጋና መለኮት አንድ ስለሆነ ነው ፤ ሥጋ አምላክ ሆነ አምላክ ሰው ሆነ ።

ክርስቶስ በሕፃንነቱ ሕፃናት ሊሠሩ የሚገባውን እየሠራና እየታዘዘ አደገ በወጣትነቱ ወይም በጐልማሳነቱ ጐልማሳ ሊሠራ የሚገባውን ከኃጢአት በስተቀር ታላላቅ ሥራ ሠርቷል ። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውንም የኃጢአት ግድግዳ አፈረሰ ። ክርስቶስ በሕፃንነቱ ይሠራ የነበረውን ሕፃናት ይሠራሉን? ክርስቶስ ለቤተ ዘመዶቹ እየታዘዘ በመንፈስ በጥበብ በቁመት ያድግ እንደነበረ ተረድተናል። እንደዚሁም ሁሉ ለአባት ለእናት የሚታዘዙ ሕፃናት በመንፈስ በጥበብ እንደሚያድጉ አይጠረጠርም የእግዚአብሔርም ጸጋ ከሕፃናት ጋር እንደሆነ የታወቀ ነው ። ስለዚህ ሕፃናት ግብረ ገብነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። እንደ ክርስቶስ ከሕፃንነት እስከ አዋቂነት፤ ከአዋቂነትም እስከ መጨረሻ ዓላማን አለመሳት የእግዚአብሔርን መንፈስና ጥበብን ያሳድራል ድል አድራጊነትንም ያሰጣል ።

ገብረ ሚካኤል ብሩ ።



## ምዕራፍ ፭

### ይህ ነው የምወደው ልጄ ፥ እሱን ስሙት ።

ቅዱስ ዮሐንስ የክርስቶስ ፊታውራሪ ፤ መንገድ ጠራጊ ፤ አዋጅ ነጋሪ በመሆኑ ከክርስቶስ በፊት ቀደም ብሎ የሰማይና የምድር ገዢ የሆነው ክርስቶስ ይመጣልና መንገዱን አስተካክሉ ፤ ጥርጊያውንም አሳምሩ ፥ ተራራው ዝቅ ይበል ፤ ጐድጓዳውም ይሞላ ፤ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ በኃጢአታችሁ ተጸጽታችሁ ለንስሓ የሚያበቃ ሥራ ሥሩ እያለ ሳይፈራና ሳያፍር ያስተምርና ያጠምቅ ነበር ። ሕዝቡም የዮሐንስ ትምህርት አስደናቂና አስገራሚ ስለሆነባቸው ፥ እንደ አምላክ ያዩት ነበር ። ዮሐንስ ግን ከተሰጠው ክብር በላይ ውዳሴ ከንቱን የማይሻ ፤ ፈጣሪውን የሚፈራ በመሆኑ አምላክ አይደለሁም የአምላክ ባሪያ መንገድ ጠራጊ ስለሆንኩ አማናዊውን ጥምቀት እስከ ምታገኙ ድረስ ለንስሓ የሚያበቃ ጥምቀት አጠምቃችኋለሁ ከኔ በኋላ የሚመጣው ግን የሁላችን ገዢ የሁላችንም ፈጣሪ ነው ። እሱ ሰማያዊ እኔ ምድራዊ ነኝ ፤ እሱ ከኔ ይበልጣል ፤ እኔ እንኳን ከሱ ልተካከል የጫማውን ማዘቢያ ለመፍታት አልችልም ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለሙን ኃጢአት ለማስወገድ ወደ ዓለም መጥቶአልና ፤ ልጅነትን ታገኙ ዘንድ በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል እያለ አምላክነቱን ይመሰክር ነበር ።

ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ፍቅር አገብሮት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ፥ ለዘመዶቹ እየታዘዘ በሰው መጠን በየ ጥቂቱ አደገ ። ከኃጢአት በቀር ሁሉንም ፈጸመ ። ፴ ዓመትም ሲሞላው ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ፤ መላእክት ሊቃነ መላእክት የሚሰግዱለት ፥ የንጉሦች ንጉሥ ፥ የገዢዎች ገዢ ፤ የሁሉ አምላክ ሲሆን ትሕትናን ለመፈጸም የዕዳ ደብዳቤያችንን በጥምቀቱ ለመደምሰስ አንድነቱንና ሦስትነቱን ለመግለጥ በባሪያው በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ፤ በሰይጣን ቅንዓት የተጻፈው ዕብነ ሩካብ የሚወገደው በጥምቀቱ ስለሆነ ክርስቶስ ጽድቅን እንፈጽም ዘንድ ይገባናልና አጥምቀኝ ብሎ ዮሐንስን አዘዘው ። ምሥጢረ ጥምቀቱም በእንዴት ያለ ሁናቴ እንደተፈጸመ ለመረዳት ብንፈልግ ፤ በማቴዎስ ወንጌል እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን ፤ በዚያ ጊዜ ኢየሱስ ከዮሐንስ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ፤ ዮሐንስ ግን እኔ ካንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጂ አንተ ወደኔ ትመጣለህን ? ብሎ እምቢ አለው ።

ኢየሱስም መልሶ እንዲሁ ጽድቅን ሁሉ እንፈጽም ዘንድ ይገባናልና አሁንስ ተው አለው ከዚያ ወዲያ እሺ ብሎው አጠመቀ ። ኢየሱስም ከተጠመቀ ። በኋላ ያን ጊዜውኑ ከውኃው ወጣ ። እንሆ ሰማዮችም ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት አየ። እነሆም ይህ ነው የምወደው ልጄ በእርሱ ደስታዬን የማይበት የሚል ድምዕ ከሰማይ መጣ ይላል ማ፥ ቴ፥ ፫፥ ፲፫—፳፯ በወንጌሉ እንደምንረዳው ክርስቶስ ጽድቅን ሁሉ እንፈጽም ዘንድ ይገባናልና አጥምቀኝ ብሎ በመጠመቁ ሥርየተ ኃጢአትን አግኝተናል በጥምቀቱ ቀድሶናል ክርስቶስ የተጠመቀው የኛን ኃጢአት ለማስወገድ ነው እንጂ ፤ ኃጢአት ኖሮበት አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰማያዊ ኢየሱስ ክርስቶስ መሬታዊ በሆነው በዮሐንስ እጅ የተጠመቀው እኛን ከሞት ወደ ሕይወት ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሐሳር ወደ ክብር ሊመልሰንና በጥምቀት በርነት ወደ ወንጌል ብርሃን ለመግባት እንድንችል ነው ። የዓለሙ ብርሃን ክርስቶስ



ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀና መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል እንዳረፈበት

ጽድቅን እንፈጽም ዘንድ ይገባናል ብሎ ከውኃው ሲወጣ አብ በደመና ሆኖ ይህ ነው የምወደው ልጄ እሱን ስሙት የሚለውን ቃል ተገንዝበን እንደ ዮሐንስ የመጀመሪያውን ምስክርነት መስጠት ፤ ቃሉን መስማት ይገባናል ፤ የታዘዝነውን የወንጌልን ቃል ጠብቀን ልጆቼ ወዳጆቼ ለመባል ካልበቃን አምነን ተጠምቀናል ፤ ተምረናል ብለን በወሬ ብቻ ጊዜውን ካሳለፍነው የምንሰጠውም የምናገኘውም ጥቅም አጥጋቢ ሊሆን አይችልም ፤ በጥምቀት ልጅነት የ ተቀበልን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነው ሰውነታችንን የተቀደሰ ሥራ በመሥራት ለጽድቅ የተዘጋጀ ፤ ከኃጢአትና ከተንኮል የራቀ ማድረግ የእየአንዳንዳችን ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል ።



ስለዚህ በጥምቀቱ እውነተኛ ልጅነት አግኝተን የመንግሥቱ ወራሾች እንድንሆን ለመልካም ሥራ እንሽቀዳደም ፤ ኢሳይያስም እነሆ የመረጥኩት ልቡናዬ የተቀበለችው ነፍሴም የወደደችው ወዳጄ (ልጄ) ለአሕዛብ ፍርድን ይፈርዳል አይጮህም አይቆጣም ፤ እውነት ፈርዶ ያድናል ፤ የሰውንም ልቡና በትምህርት ያበራል ፤ አሕዛብም በስሙ ያምናሉ ይላል ፤ ኢሳ. ፵፪ ቍ. ፩—፬ ይህ የትንቢት ቃል አብ በደመና ሆኖ ይህ ነው የምወደው ልጄ እሱን ስሙት ከሚለው ቃል ጋር የተመሳሰለ ነው ፤ በየትንቢቱም ፍጻሜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙን ያሥረዳል ፤ የሰውንም ልቦና በትምህርት ያበራል ፤ እውነት ፈርዶ ያድናል ፤ አሕዛብም በስሙ ያምናሉ የሚለውም ቃል በኋለኛው ዘመን የወንጌልን ትምህርት ተቀብለው በክርስቶስ አምነው የሚጠመቁ ክርስቲያኖች መገኘታቸውን ሲገልጥ ነው ።

በጠቅላላው የክርስቶስ መጠመቅ ለኛ ድህነት ስለሆነ ከፍዳና ከኃጢአት የምንድንበትን አማናዊ ጥምቀት አምነን መቀበል ይኖርብናል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፯ ።

## ክ ር ስ ቶ ስ ከ ተ ጠ መ ቀ በ ኋ ላ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ እንደገና ከዮሐንስ ጋር እንደተገናኙና ለሕዝቡ እንዳስተዋወቀው በወንጌሉ እንረዳለን ፣ ቅዱስ ዮሐንስ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በቢታንያና በቤተ ራባ ሲያስተምር ሳለ ክርስቶስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ ፤ ከኔ አስቀድሞ የነበረው ሰው እሱ ከኔ በኋላ ይመጣል ያልኳችሁ ይህ ነው እሱ ከኔ በፊት ነበረና ፤ እኔም አላውቀውም ነበር ፤ ነገር ግን ለእሥራኤል ይገለጥ ዘንድ ፤ ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ መጣሁ ሲል መሰከረ ።

መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ከሰማይ ወርዶ ሲቀመጥበት አየሁ ፤ እኔም የማውቀው አልነበርኩም ነገር ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ሲቀመጥበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እሱ ነው አለ እኔም አይቼ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መሰከርኩ የሚል ቃል እናገኛለን፤ዮሐ. ፩. ፳፱—፴፬ ።

የክርስቶስ ፊታውራሪ ቅዱስ ዮሐንስ የሚያስተምረውን ትምህርት አቋርጦ ጌታ ብቅ ሲል ባየው ጊዜ ለሚያስተምራቸው ሕዝቦች እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ያለበት ምክንያት ምስክርነቱን የሚሰጠው ስለ ክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣት ስለ ነበር ነው ፤ እሱ እያለ በሦስተኛ መደብ ያስተማራቸውን ትምህርት በጆሮ ከመስማት በዓይን ማየት ስለሚበልጥ በጆሮአቸው የሰሙትን በዓይናቸው አይተው እንዲረዱ እነሆ ከኔ ይበልጣል ብዬ የነገርኳችሁ ይህ ነው ብሎ ለማስረዳት ነው ።

ቅዱስ ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የሚያጠምቅ ክርስቶስ መሆኑ ስለ ተገለጸለት እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ በማለት ለሚያስተምራቸው ሕዝቦች ግልጥ አድርጎ አስረዳ ፤ አምላክነቱንም መሰከረ እነሱ ግን እሱ እንዳስተማራቸው ሊረዱለት አልቻሉም ፤ ዮሐንስ ከኔ የሚበልጠው እሱ ነው በማ

www.ethiopianorthodox.org

ለቱ ደቀ መዛሙርቱ መምህራቸውን ዮሐንስን ትተው አምላክነቱን ለመረዳት ትም ህርቱንና ተአምራቱን ለማየት ክርስቶስን ተከትለው ሄደዋል ። የሄዱትም ደቀ መዛሙርት ብዙ ምሥጢራትንና ተአምራትን አይተው የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለመመስከር በቅተዋል ።

ዮሐንስ ሲነግራቸው የነበረው ሁሉ እውነት ሆኖ አግኝተውታል ፤ ዛሬም ቢሆን በጊዜያችን ደግ መምህር ከሆነ ከኔ የሚበልጥ መምህር ከእንደዚህ ያለ ቦታ አለ ብሎ ለተማሪዎቹ ካስረዳቸው ከዚያ ቦታ ሒዶ ለመማር የማያስብ የለም ።

ስለዚህ ክርስቶስ በብሩህ ገጽ እንዲቀበለን እንደ ዮሐንስ እውነት መመስከር ቅንነትና የዋሕነትን ገንዘብ ማድረግ አለብን ። አባ ተፈራ መልሴ

## ምዕራፍ ፯

## በሀገራችን የጥምቀት በዓል አከባበር ባህልና ሥርዓት

ቤተ ክርስቲያናችን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት ጥር ፲፩ ቀን በየዓ መቱ ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የጥምቀትን በዓል የምናከብረው በሚከተለው ዓይነት ነው ።

፩ኛ በዋዜማው ያለውን ዕለት እንጾማለን ፤ ይህንም ጾመ ገሀድ ብለን እንጠራዋ ለን ፤ ገሀድ ማለት መገለጫ ማለት ነው የክርስቶስ መገለጫ ስለሆነ ነው ። ይህም ዕለት የሚጾምበት ምክንያት ጥምቀት ዓርብ ረቡዕ የዋለ እንደሆነ በጥምቀት ዕለት መጾም ስለማይገባና የዓርብ ወይም የረቡዕ ጾም ስለሚሻር በዚህ ፈንታ ለውጥ ነው ፤ ግን ጥምቀት በፍስክ ቀኖች ቢውልም የገሀድ ጾም አይቀርም በየዓመቱ ይጾማል ይህም የሆነበት ኑሮ ኑሮ ሲመጣ እንዳይረሳ እየታወሰ እንዲቄይ በማለት ነው ።

፪ኛ በዚህ ዕለት ወደ ማታ አዳራችንን ታቦተ ሕጉን ጽላተ ኪዳኑን ይዘን ወደ ወን ዝ እንወርዳለን ። ስንወርድም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት መጥቶ ወደ መጠመቂያው ወደ ዮርዳኖስ መውረዱን የሚገልጥ መዝሙር እንዘምራለን መዝ ሙሩም «ሰላም» ተብሎ ይጠራል ክርስቶስ በዮርዳኖስ የተጠመቀው ከዲያብሎስ ቅኝ ግዛት አውጥቶ ሰላም ሊያደርግልን መሆኑን ለመግለጥ ነው ። ታቦት ይዘን መውረዳችን በታቦቱ ላይ ሕጉና ቃሉ ፤ ስመ ሥላሴና የሦስቱ አካላት ሥዕል ስለ አለበት ሦስቱ አካላት አብ በምስክርነት ፤ ወልድ በጥምቀት ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በመታየት በዮርዳኖስ ወንዝ እንደ ተገለጡ በምሳሌ መታሰቢያ ውን ለማክበር ነው ።

አንድ አንድ ሊቃውንት ክርስቶስ ለመጠመቅ ፤ ዮሐንስ ለማጥመቅ ፤ አብ መንፈስ ቅዱስ ለምስክርነት ብቻ ወደ ዮርዳኖስ ስለ ወረዱ የሥላሴ ፤ የኢየሱስ ፤ የዮ ሐንስ ታቦት ብቻ ወደ ባሕር ይውረዱ እንጂ ሌሎቹ መውረድ አያስፈልጋቸውም በማለት አስተያየት ያቀርባሉ ፤ ቢሆንም ማንኛውም ጽላት ስመ ሥላሴ ስለ አለበት ሁሉም መውረዳቸው አልቀረም ።



በየአንዳንዱ ክፍለ ሀገር ደግሞ ታቦት ሳይዙ በታቦት ፈንታ ወንጌል ይዘው ይወርዳሉ ። ይህም የሚደረገው ዮሐንስ ማጥመቁን ፤ ወልድ መጠመቁን ፤ አብ «ይህ ነው የምወደው ልጄ እሱን ስሙት» ብሎ መመስከሩን ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መገለጡን ጠቅላላ የጥምቀትን ታሪክ አጠቃሎ የያዘው ወንጌል በመሆኑ ቃሉን ይዞ ወርዶ መታሰቢያውን ማክበር አስፈላጊ ስለ ሆነ ነው ።

፫ኛ ከባሕር ወርደን ድንኳን ተክለን ፤ ዳስ ጥለን ቅዱስ ያሬድ ከብሉይና ከሐዲስ ከመጻሕፍተ ሊቃውንትና ከታሪክ መጻሕፍት እያወጣጣ ስለ ጥምቀት የዘመ ረውን መዝሙር እየዘመርን ፤ ማኅሌት በመቆም ጥምቀት ነክ የሆኑ መዝሙራተ ዳዊት በመዘመር ፤ ስለ ጌታ ጥምቀት የሚናገሩትን ከ፬ቱ ወንጌሎች በማንበብ መታሰቢያ ውን ስናከብር እናድራለን ። ይህንም የምናደርግበት ፤ ጥምቀት በበዓለ መጸለት የገባ ስለ ሆነ አይሁድ በዓለ መጸለትን ከቤታቸው ወጥተው ድንኳን ተክለው ዳስ ጥለው ያከ ብሩት ስለ ነበር ፤ በዚያ ባህልና ልማድ ነው ።

፬ኛ በ፲ ሰዓተ ሌሊት ቅዳሴ እንቀድሳለን ፤ ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ስለ ሆነ ነው ። ጌታችን በ፲ ሰዓት መጠመቁን የእ ስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቄርሎስ «ጥር ፲፩ ቀን በ፲ ሰዓተ ሌሊት ሁለቱ ማለት ጌታና ዮሐንስ ወደ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ሄዱ ውኃዎችም እንደ ሞቀ ውኃ ፈሉ» ሲል ይነግረናል ።

፭ኛ ከጸሎተ ቅዳሴው ኋላ በ፲፩ ሰዓት በመጽሐፈ ጥምቀት እንደተሠራው ሥር ዓት ልዑካኑ (ቀዳስያኑ) ልብሰ ተክህኗቸውን እንደ ለበሱ መዘምራኑ ጸናጽልና ከበ ሮዋቸውን እንደያዙ ምእመናኑ ሁሉ ወደ ባሕረ ጥምቀት ይሄዳሉ ፤ በዚያም ቄሱ በጥና ፍም ጸንሰ ዕጣን ያሳርጋል ፤ የነግህ ሊጦን ፤ የሌሊት መስተብቍዕ በመድገም ጸሎት ያደርጋል ። ካህናቱ ሁሉ ከመዝሙረ ዳዊት ስለ ጥምቀት የተዘመረውን ክፖ ተት እየተቀባበሉ (እያስተዛዘሉ) ይዘምራሉ ፤ የክሥተቱ ዜማ ሲያልቅ ዲያቆኑ ከመ ዝሙረ ዳዊት ስለ ጥምቀት የተዘመረውን ምዕራፍ ይመራል ፤ ካህናቱም ተቀብለው በማስተዛዘል ምዕራፉን እየተቀባበሉ ይዘምራሉ ፤ ምዕራፉ ሲያበቃ ስለ ጥምቀት በኦሪት የተነገረው ትንቢትና ምሳሌ ከኦሪት ከነገሥት ከነቢያት ይነበባል ። ከዚህ በኋላ ዲያቆኑ ከመዝሙረ ዳዊት ስለ ክርስቶስ ጥምቀት የተነገረውን ትንቢትና ምሳሌ የሚ ነካ ምስባክ ይሰብክና ጸሎተ ወንጌል ይደርሳል ። ቄሱ ስለ ጥምቀት የሚናገረውን ወንጌል ያነባል ልዩ ልዩ ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ጥምቀት ያዘ ጋጁት ጸሎት ይጸለያል ። ይህ ዓይነት ሥርዓት በ፬ቱም ማዕዝነ ባሕር ይደርሳል ።


፲፪ ሰዓት ሲሆን «እስመ ተለዓለ ስሙ» የሚለው አባ ጊዮርጊስ የደረሱት ሰዓ ታት ኵሎሙ ሠራዊተ ሰማያት የሚለውን ጨምሮ ይዘመራል ። ነግህ ሲሆን ማለት ሲነጋ አርያም ተመርቶ ይዘመራል ። ሥርዓተ ቅዳሴና ጸሎተ አኰቴት ይደርሳል ። ሥርዓተ ቅዳሴውም በጸሎተ ወንጌል ከተፈጸመ በኋላ ጸሎተ ሃይማኖት (የሃይማኖት ጸሎት) ይጸለያል ። ከዚህም በኋላ መዘምራኑ «በዝንቱ ማይ ቀድሰነ» በዚህ ውኃ

www.ethiopianorthodox.org

ቀድሰን አንጻን» የሚለውን አቡን መርተው ይዘምራሉ ፤ በኋላም የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ቅ| ሳዊሮስ በቅዳሴ ሥርዓት ዓይነት ስለ ጥምቀት የደረሰው የባሕር ጸሎት እንደ ቅዳሴው አገባብ ይጸለያል ። ጸሎተ ንስሐ (የንስሐ ጸሎት) ይደገማል ። እንደ ቅዳሴው ሥርዓት "አሐዱ አብ ቅዱስ» ተብሎ ፵፪ ጊዜ እግዚአታ ይደርሳል ።

ከዚህ ቀጥሎ ቄሱ መስቀሉን በውስጥም በውጭም በ፫ ፊት ሜሮን ይቀባና በውኃው ላይ አሐዱ አብ ቅዱስን በዜማ እያለ በትእምርተ መስቀሉ ፫ ጊዜ አማትቦ፥ ውኃዉን ይባርካል ። ውኃዉንም ከባረከ በኋላ መጀመሪያ ሕዝቡን ያጠምቃል ፤ በኋላም ካህናቱን ያጠምቃል ፤ ይህም ታላቅ ምሳሌና ምክንያት አለው፥ በባሕሩ ዳርቻ ተሰብስበን ይህን ሁሉ ጸሎት የምንጸልየውና ቃለ እግዚአብሔር የምናደርሰው በዮርዳኖስ ወንዝ «ይህ ነው የምወደው ልጄ እሱን ስሙት» የሚል ቃለ እግዚአብሔር ስለ ተነገረበትና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በውኃው ዳር ስለ ጸለየ ነው ። ሉቃስ «እሱ ሲጸልይ ሰማይ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወረደበት ፤ ድምፅም ከሰማይ መጣ አንተ ነህ የምወድህ ልጄ ባንተ ደስታዬን አያለሁ የሚል» ይላል ሉቃ ፫፥ ፳፩—፳፫ ።

በባሕሩ ላይ ስብሐተ እግዚአብሔርና ጸሎት ከደረሰበት በኋላ ቄሱ የሚባርከው ዮርዳኖስ በክርስቶስ ጥምቀት መባረኩንና መቀደሱን ለማስታወስ ነው ። ክርስቶስም



የጥምቀት በዓል አከባበር ባህልና ሥርዓት ።



«አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ፥ ውኃው ይቀደስ ይባረክ ዘንድ በውኃ አጥምቀኝ» ብሎ ነው ዮሐንስን ያዘዘው ። ውኃዉንም ከባረከ በኋላ በመጀመሪያ ሕዝቡን ፤ ቀጥሎ ካህናቱን የሚያጠምቀው ሕዝቡ ከተጠመቁ በኋላ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ስለ ተጠመቀ ነው ። ይህንንም ሉቃስ ሲያስረዳ «ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ» ብሎ ይተርካል ሉቃ፥ ፫፥ ፳፩ ።

ይህን በየዓመቱ የምንጠመቀውን ጥምቀት በመመልከት አንድ አንድ ሰዎች ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ይጠመቃሉ ይሉናል ። ይህ ምሥጢሩ ሳይገባቸው ቀርቶ ነው እንጂ ሁለተኛ ለመጠመቅ አይደለም፤ የጌታችንን ጥምቀት መታሰቢያ ለማስታወስ ነው ። በጠቅላላው የጥምቀትን በዓል ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ሥነ ሥርዓት አክብረን፥ በመዝሙር፤ በሽብሸባ ፤ በጭብጨባ ፤ በሆታ በዕልልታ ታቦቶቹን አጅበን ይዘን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንመለሳለን ።

## ምዕራፍ ፰

### እኛ የምንጠመቀው ጥምቀት ።

እኛ የምንጠመቀው ጥምቀት በሁለት ታላላቅ ክፍል ይከፈላል ።

፩ኛ| ጥምቀተ ኦሪት (ጥምቀተ ንስሐ)

፪ኛ| ጥምቀተ ወንጌል (ጥምቀተ ክርስቶስ) ነው ።

### ፩ኛ| ጥምቀተ ንስሓ

የኦሪቱ ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት ነበር ፤ አንድ ሰው የኦሪትን ሕግ ተላልፎ ኃጢአት የሠራ እንደሆን ሲመለስ በውኃ ይጠመቅ ነበር ። ዘሌ፥ ፲፭፥ ፰ ። አንድ አሕዛብ በኦሪት አምኖ ወደ አይሁዳዊነት ሲገባ ፡ ይህን የንስሓ ጥምቀት ይጠመቅ ነበር ። ማቴ፥ ፳፫) ፲፭ ። እሥራኤል ባሕረ ኤርትራን መሻገራቸው ጥምቀታቸው፤ ነበር) ። ፩ኛ፥ ቆሮ፥ ፲፥ ፪፥ ።

መጥምቁ ዮሐንስ ሲያጠምቀው የነበረው ጥምቀት የኦሪቱ የንስሓ ጥምቀት ነበር፤ (ማቴ ፫ , ፲፩) ። የጌታም ደቀ መዛሙርት ይህን የንስሓ ጥምቀት አልፈው አልፈው አጥምቀዋል በዚህ ጥምቀተ ንስሓ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ጥምቀተ ቄደር ገብቷል። አሁንም ይሠራበታል ማለት ይቻላል አላማው ያው ጥምቀተ ንስሓ ነው ። አዲሶች አማንያን ለዐቅመ አዳምና ሔዋን ከደረሱ በኋላ ንስሓ ገብተው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለመጠመቅ ሲፈልጉ በመጀመሪያ የሚጠመቁት ይህን ጥምቀተ ቄደር (የንስሓ ጥምቀት) ነው ። ያለፈው ኃጢአታቸው በዚህ ጥምቀተ ቄደር እንዲነፃ ነው ። ሕፃናት ግን ኃጢአት ስለሌለባቸው የንስሓ ጥምቀት ሳይጠመቁ የልጅነት ጥምቀት ብቻ ይጠመቃሉ ፤ ከአመኑ ከተጠመቁም በኋላ ብዙ ኃጢአት ሲሠሩ የኖሩ ፤ ክርስቶስን ክደው በአረማዊነት በእሥልምና በአምልኮ ጣዖት የቄዩ ሰዎች እንደገና አምነው በንስሓ ሲመለሱ ጥምቀተ ቄደር ይጠመቃሉ ። ይህ ጥምቀተ ቄደር ይደገማል ።

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአተኞች ይህን ጥምቀት የሚጠመቁት፣ ለቀሳውስት ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ነው ። ይህም ዮሐንስ የንስሓ ጥምቀት ሲያጠምቅ ሕዝቡ ከእሱ የሚጠመቁት፣ በመጀመሪያ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙለትና እየነገሩት ስለ ነበር ነው (ማቴ ፫|፮) ። ሐዋርያትም ሲያጠምቁ፣ የሚያጠምቋቸውን ሰዎች እንዲያምኑ ፤ ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙ፤ ንስሓ እንዲገቡ ፥ ይጠይቋቸው ነበር ። (ዮሐ. ፪ ፹፩ ። ፲ ፴-፴፰ ። ፲፰ ፰) ።

## ሁለተኛ ጥምቀተ ክርስቶስ ።

ጥምቀተ ክርስቶስ ወይም የልጅነት ጥምቀት የሚባለው ፥ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ያስተማረው ፥ ሐዋርያት እንዲያጠምቁ ያዘዛቸው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው ። ማቴ ፫ , ፲፩ ። ዮሐ ፫ , ፳፪ ። ፬ , ፩፡ ፪ ።

ይህ የክርስቶስ ጥምቀት ከሥላሴ ልጅነትን ያሰጣል፤ መንግሥተ ሰማያት ያገባል ኃጢአት ያስተሠርያል ። (የሐ. ሥ. ፪ , ፴፰) ። ይህ የልጅነት ጥምቀት ሁለተኛ ልደት ተብሎ ተተርጒሟል (ዮሐ. ፫ , ፩-፮ ። ቲቶ ፫ ፭ ) ። ይህ የክርስቶስ ጥምቀት እንደ ጥምቀተ ቄደር አይደለም፤ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚፈጸመው ። ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ «ጥምቀት አንዲት ናት» ስለ አለና መቅዶንዮስን በቍስጥንጥንያ ጉባኤ ያወገዙት ፩፻፶ ሊቃውንትም «ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ፡— በአንዲት ጥምቀት እናምናለን» ብለው ስለወሰኑ ነው ። (ኤፌ ፬ , ፭-፮) ። ዮሐንስ አፈወርቅም በ፲፫ኛው ተግሣጹ « ጥምቀት አንዲት ናት እንጂ ሁለተኛ ጥምቀት የለም» ብሎ የጻፈው፣ ስለ ልጅነት ጥምቀት አለመደገም ሲያስረዳ ነው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፱

## ከመጠመቃችን በፊት የምንፈጽማቸው

አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት ፩ኛ| ማወቅ ፤ ፪ኛ| ማመን ፤ ፫ኛ| ንሰሓ መግባት አለበት ይህም የሚያስፈልገው ካደጉ በኋላ ለሚጠመቁ ኃጢአት ለሠሩ ሰዎች ነው እንጂ ለሕፃናት አይደለም ሕፃናት ግን የሠሩት ኃጢአት ባለመኖሩና ለዕውቀት ባለመድረሳቸው፣ ይህ ሥርዓት አያስፈልጋቸውም ።

ቢሆንም ወላጆች ሕፃናትን ክርስትና ሲያስነሡ፣ ቤተ ክርስቲያን ዋስ ታስጠራቸዋለች ፤ እነዚህም ዋሶች «የክርስትና አባትና እናት» ይባላሉ እነሱም ለሕፃናቱ ሃይማኖት ከባድ ኃላፊነት አለባቸው ሕፃናቱ በሃይማኖት እንዲጸኑ ፤ በግብረ ገብነት እንዲያድጉ ማስተማርና መቈጣጠር ዓይነተኛ ሥራቸው ነው ። ከላይ እንዳልነው ትልልቆቹ ግን ይማራሉ ፤ ያውቃሉ ፤ ያምናሉ ፤ ንስሓም ይገባሉ ፤ ለተወሰነም ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ የሃይማኖት ጸሎት ያጠናሉ ሕጉንና ሥርዓቱንም ይመለከታሉ፤ በመጀመሪያ የሚጸልዩት ጸሎት» በስመ አብ» ነው እስኪ ጠመቁ ድረስ» ፃዑ ንዑሰ ክርስቲያን» ሲባል ይወጣሉ። ንዑሰ ክርስቲያን (የክርስቲያን ታናናሾች) የሚባሉት እነዚህ ናቸው ።



## ም ዕ ራ ፍ ፲

## የጥምቀትን ዘመን ዕድሜ አይገታውም

አንድ አዲስ አማኝ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የክርስቶስን መውረድ መወለድ መሞት መነሣት ማረግ ዳግመኛ መምጣት ዐውቆ ካመነ ንስሓ ከገባ ለመጠመቅ ዕድሜው አይከለክለውም ። ሐዋርያት ያጠምቋቸው የነበሩት ትልልቆችም ሕፃናትም ናቸው (የሐ. ሥ. ፪፡ ፴፱፡ ፲፡ ፴፫ ። ፩ኛ| ቆሮ ፲፡ ፲፮) ። ፍትሐ ነገሥትም ትልቁም ትንሹም ሳይለይ ይጠመቅ ይላል ። አንድ አንድ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስ የተጠመቀው በ፴ ዓመቱ ነውና በ፴ ዓመት መጠመቅ አለብን ፤ ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎዋልና ስለ እምነት አጥንተን ሳናውቅና ሳናምን መጠመቅ አይገባንም እያሉ የኛ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን ስታጠምቅ ይነቅፉዋታል ። ነገር ግን ከላይ እንዳልነው ሐዋርያት ሲያጠምቁ መላውን ቤተ ሰብ ዐዋቂዉንም ሕፃኑንም ነበር እንጂ ዐዋቂዉን ብቻ እየመረጡ አልነበረም ።

ቅዱስ ጴጥሮስም በመጀመሪያ ካጠመቃቸው ክርስቲያኖች መካከል ሕፃናትም ነበሩ ። ኤሬኒዎስም የተባለው ሊቅ «ክርስቶስ ሁሉን ለማዳን መጥቷል ሁሉም ልጆችም ሕፃናትም ወጣቶችም ጐልማሶችም ሽማግሌዎችም ከሱ በጥምቀት ይወለዳሉ ስለዚህ በዕድሜ መካከል አለፈ ሕጻናትን ለመቀደስ ሕፃን ሆነ ወጣቶችንም ለመቀደስ ወጣት ሆነ ጐልማሶችንም ለመቀደስ ጐልማሳ ሆነ ሁሉንም ይቀድስ ዘንድ በሁሉ መጠን ሆነ ስለዚህ ሕፃናትን ወደ ክርስቶስ ታመጧቸው ዘንድ ይገባል ጌታ ሕፃናትን ተዋቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉዋቸው መንግሥተ ሰማያት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና» ብሏልና ይላል (ለመናፍቃን በጻፈው መጽሐፍ ም. ፪፡ ቍ. ፳፪) የእኛ ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያኖቹን ልጆች ወንዶቹን በ፵ ቀን ሴቶቹን በ፹ ቀን ታጠምቃለች ። አዲስ አማኒ ከሆነ ግን በ፻ ዓመቱም ቢመጣ ታጠምቃለች እንጂ አትከለክለውም ።

ሕፃናትን በ፵ና በ፹ ቀን የምታጠምቀው ግን ምሳሌ ይዛ ነው ።

፩ኛ| መጽሐፈ ኩፋሌ እንደሚነግረን አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ ሔዋን በተፈጠረች በ፹ ቀኑዋ ከሥላሴ ልጅነትን አግኝተው ገነት ገብተዋል ።

፪ኛ በሕገ ኦሪት ወላጆች ወንድን ልጅ በ፵ ቀኑ ፤ ሴትን ልጅ በ፹ ቀኑዋ ለመሥዋዕት የርግብ ጫጩት ፤ የቍርዬ ልጅ ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ለካህኑ አቅርበው፣ ያስባርኩዋቸው ነበር ። ጌታም ይህን ሕግ ፈጽሞታል ። ቤተ ክርስቲያናችን በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተነገረው የሕፃናትን ጥምቀት ከመቀበሏም በላይ ፥ ጊዜ ወስና ማጥመቋ ያስመሰግናታል እንጂ አያሳማትም ።

## ተጠማቂዎች ወደ አጥማቂዎች ስለመሄዳቸው።

ምንም እንኳ በወንጌል ሂዳችሁ አስተምሩ አጥምቁ» ተብሎ ቢታዘዝ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ለመጠመቅ የወደዱ ተጠማቂዎች (ክርስትና የሚነሡ) ወደአጥማቂዎች ሂደው ነው እንጂ አጥማቂዎቹ (ቀሳውስቱ) ወደ ተጠማቂዎቹ ሂደው አይደለም ። የዚህም ሥርዓት ምንጩ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አጥማቂው ወደ ዮሐንስ ሂዶ፣ መጠመቁ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ጌቶች በድሆች እጅ ስለመጠመቃቸው፡

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ጌቶች ነገሥታት መሳፍንት ፤ መኳንንት ታላላቅ ሰዎች ሁሉ በድሆች ክህናት ዕጅ ይጠመቃሉ እንጂ እንደ እነሱ ጌታ የሆነ ክህን ፈልገው አይጠመቁም። የዚህም መሠረቱ የጌቶች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ የአማልክት አምላክ ልዑል እግዚአብሔር በባሪያው በፍጡሩ በዮሐንስ እጅ መጠመቁ ነው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፲፩

## ሥርዓተ ጥምቀት

ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸመው በቤተ ክርስቲያን ነው ። በውኃው ላይ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሥርዓተ ቅዳሴ ያደርሱበታል፤ ጸሎት ይጸልዩበታል፤ መዘምራን አርያም ይዘምሩበታል ።

### ሰዎች ከመጠመቃቸው በፊት የሚጸልዩት ወይም የሚመሰክሩት የእምነት ማረጋገጫ ።

ለዐቅመ አዳም ወይም ለዐቅመ ሔዋን የደረሱ አዲሶች አማኞች ከመጠመቃቸው በፊት «ጸሎተ ሃይማኖት» የተባለውን የሃይማኖት ጸሎት ይጸልያሉ እምነታቸውንም በአፍ ይመሰክራሉ ያረጋግጣሉ ። በ፵ና በ፹ ቀን የሚጠመቁ ሕፃናት ግን መናገር ስለማይችሉ የክርስትና አባታቸው ወይም እናታቸው (ዋሶቻቸው) ጸሎተ ሃይማኖትን ይደግሙላቸዋል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፲፩

## ም ሥ ጢ ረ ጥ ም ቀ ት

እኛ የምንጠመቅበት ውኃ ቄሱ በባረከው ጊዜ ተለውጦ በዕለተ ዓርብ ከጌታ ጐን የፈሰሰውን ማየ ገቦ ይሆናል ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን እኛ በሞቱ እንደ ተጠመቅን ይህን ዕወቁ» ይላል ሮሜ. ፮.፫. ። በመልእክተ ዮሐንስ ቀዳማዊም በውኃና በደም በመንፈስም እንደመጣ በውኃ ብቻ አይደለም በውሀም በደምም በመንፈስም ነው እንጂ የእውነት መንፈስ እንደመሆኑ የሚመሰክር ነው ፤ የሚመሰክሩ መንፈስና ማይ ደም እነዚህ ፫ቱ ናቸው ። ፫ቱም አንድ ናቸው ፤ ተብሎ ተጽፎዋል ። ም. ፭ ፡ ፮–፱ ።

ይህ ጥቅስ የሚያስረዳው ከጌታ ጐን በዕለተ ዓርብ በፈሰሰው ደምና ውኃተጠምቀን መንፈስ ቅዱስን መቀበላችንን ነው ። ዮሐንስ በጥምቀት የምናገኘውን ሦስቱንም ነገሮች መደዳውን ተናግሮአቸዋል ። ግን ውኃዉ ተለውጦ ማየ ገቦ ሲሆንና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ሲያሰጥ ባለመታየቱ ምሥጢር ተብሏል የሚታየው በረቂቁ ዓይን በእምነት ብቻ ስለ ሆነ ነው ።



## ም ዕ ራ ፍ ፲፪

## የምንጠመቅበት ውኃ ምን ዓይነት እንደ ሆነና የአጠማመቁ ሥነ ሥርዓት

ማጥመቅ የሚገባው በፈሳሽ ውኃ ነው ። ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በታለቁ ፈሳሽ ጅረት በዮርዳኖስ ስለ ሆነ ነው ማቴ፤ ፫፤ ፩፫ ። ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን መስፍን ያጠመቀው በፈሳሽ ውኃ ነው። የሐ፤ ሥ፤ ፰፤ ፴፮፤ ፴፰፤ በዚህ



ኢትዮጵያዊው መስፍን በሠረገላ ሲሄድ ፊልጶስ ትንቢቱን እንደተረጐመለትና እንዳጠመቀው

መሠረት የሥርዓት መጻሕፍቶቻችን ጥምቀትን የሚጠመቁ ሁሉ በፈሳሽ ውኃ እንዲጠመቁ ፥ ያዛሉ ። ዲዲስቅልያ ጥምቀት በፈሳሽ ውኃ እንዲሆን ፥ ያም ባይሆን ፫ ጊዜ በተጠማቂው ራስ ላይ እንዲፈስበት» ይላል ። ዲዲስቅልያ እንደሚያዘው በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በሌላ ቦታ ተጠማቂዎች ስለሚበዙና ቤተ ክርስቲያኖችም የተሠሩት አብዛኞች ውኃ በማይገኝበት በየተራራው ስለሆነ በመርጨት ወይም ጥቂት ውኃ በሰውነታቸው ላይ በማፍሰስ ይጠመቃሉ ። ይህም ዓይነት ሥርዓት ቀደም ብሎ በትንቢተ ሕዝቅኤል «የጠራ ውኃ አፈስባችኋለሁ ትጠራላችሁ ተብሎ ተነግሮዋል ሕዝ ፴፮፤ ፳፭ ስለዚህ በመርጨት ወይም በማፍሰስ ማጥመቅ በመጽሐፍ ያለ ሥርዓት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ተጠማቂው የሚጠመቀው በማፍሰስ ወይም በመርጨት ካልሆነ ግን ፫ ጊዜ ከውኃው በመጥለቅና በመውጣት ይጠመቃል ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመቃብር ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው ሮሜ ፮ ፫-፬ ።

## ምዕራፍ ፲፫ ።

## አ ጥ ማ ቂ ው

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት አጥማቂው ሁል ጊዜ ጳጳስ ወይም ቄስ ብቻ ነው ይህም የቅስናን ሥልጣን ከጌታ የተቀበሉ ሐዋርያት ያጠምቁ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያስረዳ ነው ። ነገር ግን አስፈላጊ ሁኖ ከተገኘ ዲያቆናት፣ ሕዝባዊ ሴት ሳትቀር ሊያጠምቁ እንደሚችሉ በሊቃውንት ይታመናል ። በኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህ ገና አልተወሰነም ካህናት በማይገኙበት ሀገር አጥምቁን አምነናል እያሉ አቤቱታቸውን የሚያቀርቡት በዝተዋል ። ሊታሰብበትና በተቀዳሚ ሊወሰን የሚገባው ሥርዓት ነው። የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት ወስነው ፣ ከሲኖዶሳቸው አግብተውታል ። ዲያቆናት ያጥምቁ ብለው የወሰኑትም ዲያቆኑ ፊልጶስ ኢትዮጵያዊዉን ባለሥልጣን ማጥመቁን በመመልከት ነው ።

## ምዕራፍ ፲፬ ።

## በማን ስም ነው የምናጠምቀው ?

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ስናጠምቅ አጠምቀከ በአብ ፤ አጠምቀከ በወልድ አጠምቀከ በመንፈስ ቀዱስ ፣ በአብ ስም አጠምቅሀለሁ ፤ በወልድ ስም አጠምቅሀለሁ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሀለሁ ። እያልን በሦላሴ ስም ነው የምናጠምቀው ።

ይህንም የምናደርገው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁዋቸው። ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አዘዘን ነው ማቴ ፳፰ ፣ ፲፱ ። ሐዋርያት በክርስቶስ ስም ያጠምቁ ነበር ( የሐ. ሥ ፪ ፣ ፴፰ )። በኋላ ግን እንደ ትእዛዙ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ ቀስ በቀስ ሥርዓት ሁኖ ፣ ተይዞዋል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፲፭ ።

## የሐዲስ ጥምቀት ዓይነት ።

የአሪቱ የንስሓ ጥምቀት ሳይጨመር ፣ የሐዲሱ የክርስቶስ ጥምቀት ብቻ ፫ ዓይነት ነው ።

፩ኛ የውኃ ፤
፪ኛ የደም ፤
፫ኛ የአሳብ ጥምቀት ነው ።

፩ኛ የውኃ ጥምቀት የሚባለው እስከ አሁን የተናገርነው ልጅነትን የሚያሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው ።



፪ኛ የደም ጥምቀት የሚባለው አንድ ሰው አምኖ ንስሐ በመግባትና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በማጥናት ላይ ሳለ ሳይጠመቅ ድንገት ፈጣሪህን ካድ ፤ ለጣዖት ስገድ የሚል ግዳጅ ገጥሞት ለጣዖት አልሰግድም ፈጣሪዬን አልክድም ብሎ በሰማዕትነት የሞተ እንደሆነ ደሙ ከጥምቀት ይቈጠርለታል ይባላል ። ይህ ዶክትሪን በብዙዎች ሊቃውንት ተደግፎዋል ።

፫ኛ ፤ የአሳብ ጥምቀት የሚባለው አንድ ሰው አምኖ ለመጠመቅ ፈልጎና አስቦ አሳቡ ሳይፈጸምለትና ሳይጠመቅ ድንገት ቢሞት ፣ አሳቡ እንደ ጥምቀት ይሆነዋል ይባላል ። ይህም እንደ ፈያታይ ዘየማን ማለት ነው ። ቢሆንም ይህ አስተያየት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንጂ ፣ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ስፍራ አላገኘም ።

ክንፈ ገብርኤል አልታዬ

## ም ዕ ራ ፍ ፲፮ ።

የኢትዮጵያ አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት በምታከብርበት ዕለት የምትዘምራቸው ከቅዱስ ያሬድ የተደረሱ መዝሙሮች ፤ ከመዝሙረ ዳዊት የተውጣጡ ምስባክትና ከሐዲሳት መጻሕፍት የተውጣጡ ምንባባት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

### ፩ ኛ ዋ ዜ ማ ።

ሐዳፌ ነፍስ ለጻድቃን ፤ ወተስፋ ቅቡፃን ክርስቶስ አስተርአየ ውስተ ዓለም ፤ እምድንግል ተወልደ ፤ ከሡተ ኮነ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ ፣ ከዊኖ ሰብአ ፤ በዮርዳኖስ ተጠምቀ ።

### ትርጉም

የጻድቃንን ነፍስ የሚያሻግር ፤ ተስፋ የቈረጡ ተስፋ ክርስቶስ በዓለም ታየ ፤ ከድንግል ተወለደ ፤ ሰው ሆኖ ለዘመዶቹ እየታዘዘ በማደጉ ግልጥ ሆነ ፤ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ።

### ፪ኛ በሃምስት ።

በዮርዳኖስ ተጠምቀ ፈጺሞ ሕገ ፤ ወስተርአየ ገሀደ ፤ በዮርዳኖስ ተጠምቀ ።

### ትርጉም

ክርስቶስ ሕግን ፈጽሞ ፣ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፣ በግልጽም ታየ ።

### ፫ኛ እግዚአብሔር ነግሠ ።

አስተርእዮ ኮነ ዘክርስቶስ ሥነ መለኮት ከመ ርግብ ውስተ ምጥማቃት እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ።

### ትርጉም

አብ በመጠመቂያው ውስጥ የምወደው ልጄ ይህ ነው ሲል የክርስቶስ መገለጥ ሆነ፤ የመለኮት መልክ (መንፈስ ቅዱስ) እንደርግብ ወይም በርግብ ምሳሌ ተገለጠ ።

### ፬ኛ በሃምስት ።

አስተርአየ ዘኢያስተርኢ ፤ ወርኢነ ብዕለ ስብሐቲሁ ፤ አስተርአየ ዘኢያስተርኢ።

www.ethiopianorthodox.org

ትር ጕም

የማይታየው (አምላክ) ታየ ፤ እኛም የክብሩን ባለጸግነት አየን ።

፫ኛ ይትባረክ

ርእዩከ ማያት እግዚኦ ፤ ርእዩከ ማያት ወፈርሁ ፤ ደንገጹ ቀለያተ ማያት ፤ ወደምፀ ማያቲሆሙ ።

ትርጕም ፤

አቤቱ ውኃዎች አዩህ ፤ አይተውህም ፈሩ ፤ የውኃዎቹም ወንዞች ደነገጡ ፤ ፈሳሾቻቸውም ተሰሙ ።

፬ኛ ሰላም ፤

በሰላም አስተርአየ ወልደ አምላክ ፍጹም ፤ ወተወልደ በሀገረ ዳዊት ፤ በዮርዳኖስ ተጠምቀ ከመ ይቤዝወነ ፤ ወልደ አምላክ ፍጹም አስተርአየ ።

ት ር ጕ ም ፤

የፍጹም አምላክ ልጅ በሰላም ተገለጠ ፤ በዳዊትም አገር ተወለደ ፤ እኛን ያድነን ዘንድ ፥ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ።

፭ኛ ክብር ይእቲ፥

ኵሎሙ ማኅበረ መላእክቲሁ ይሴብሑ ወይዜምሩ ለዘበሥጋ ሰብእ አስተርአየ፤ ንዑ ንስግድ ሎቱ ፤ ሃሌ ሉያ ።

ት ር ጕ ም ፤

የመላእክቱ ማኅበር ሁሉ ከዓለም በፊት ለነበረ ና ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ፤ በሰው ሥጋ ለተገለጠ (አምላክ) ይዘምራሉ ፤ ያመሰግኑታልም ። እኛም ኑ እንስገድለት ።

፮ኛ ዝ ማ ሬ ፤

ኅብስተ ሰማያዌ ወጽዋዐ ዘእማየ ሕይወት ጠዐሙ ፥ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ።

ት ር ጕ ም ፤

እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ በመንፈስ ቅዱስ ታውቁ ዘንድ ፤ ሰማያዊዉን ኅብስትና ከሕይወት ውኃ የተመላውን ጽዋ ቅመሱ ።

፯ኛ ዕጣነ ሞገር ፤

ወደሞ ክቡረ መንፈሰ ሕይወት ወቅድሳተ መንፈስ ወሀበነ ወማየ መንጽሒ ዚአነ ።

ት ር ጕ ም ፤

የሕይወት መንፈስ የሆነውንና በመንፈስ የተቀደሰውን ክቡር ደሙን ፤ እኛን የሚያነጻ ውኃ ማለት ጥምቀትን ሰጠን ።

፲ኛ ወደ ባሕር መውረጃ ሰላም

ወረደ ወልድ እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት በፍሥሓ ወበሰላም ።



ት ር ጕ ም ፤

ወልድ በደስታና በሰላም ከሰማያት ወደ መጠመቂያ ቦታዎች (ዮርዳኖስ) ወረደ ።

፲፩ኛ የቅኔ ማኅሌት ምስባክ ፤

ባሕርኒ ርእየት ወጐየት ፤
ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ ፤
አድባር አንፈርዓፁ ከመ ሐራጊት ።

ት ር ጕ ም ፤

ባሕር አይታ ሸሸች ፤ ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ ፤ ተራራዎች እንደጊደሮች ዘለሉ ።

፲፪ኛ ወንጌል ፤

ማቴዎስ ም| ፫. ፲፫ ፍጻሜ ። «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከዮሐንስ ይጠመቅ ዘንድ፥ ከገሊላ ወደዮርዳኖስ መጣ ። ዮሐንስ ግን እኔ ከአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል ፤ አንተም ወደኔ ትመጣለህን » ብሎ እምቢ አለው ። ኢየሱስም መለሰለት ፥ እንዲሁ «ጽድቅን ሁሉ እንፈጽም ዘንድ ይገባናልና አሁንስ ተው አለው» ። ከዚያም ወዲያ እሺ ብሎ ተወው ። ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ፥ ያን ጊዜውን ከውኃ ወጣ ። እነሆ ሰማዮችም ተከፈቱ ። የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደርግብ ወርዶ ፥ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየ ። «እነሆም ይህ ነው የምወደው ልጄ በሱ ደስታዬን የማይበት የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ ።

፲፫ኛ አንገርጋሪ ፤

ክርስቶስ ተወልደ ፤ ክርስቶስ ተጠምቀ ፤ ወለደነ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ እሙነ ከነ ለፀሐየ ጽድቅ አስተርእዮቱ ፤ አማን መንክር ስብሓተ ጥምቀቱ ።

ት ር ጕ ም

ክርስቶስ ተወለደ ፤ ክርስቶስ ተጠመቀ ፤ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ሁለተኛ ወለደን ፤ የፀሐየ ጽድቅ (ክርስቶስ) መገለጽ የታመነ ሆነ ፤ የጥምቀቱ ምስጋና (ክብር) በእውነት ዕፁብ ድንቅ ነው ።

፲፬ኛ እስመ ለዓለም

ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ ከመ ያጥምቆ በፈለገ ዮርዳኖስ ፤ ወወጺኦ እማይ ተርኅወ ሰማይ ። መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ሎቱ ስምዕዎ ።

ት ር ጕ ም

በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቀው ዘንድ ፤ ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዮሐንስ ሄደ ፤ ከውኃውም ከወጣ በኋላ ፥ ሰማይ ተከፈተ ከደመናውም የምወደው ልጄ ይህ ነው እሱን

www.ethiopianorthodox.org

ስሙት የሚል ቃል መጣ ።

### ፲፫ኛ ዕዝል ።

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ፤ ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ፤ ወተገሠ በሥጋ መንፈስ ዘኢይትገሠሥ ወዘኢይትለከፍ ዘመልዕልተ ሰማያት ዘመልዕልተ ሥልጣናት ወገብረ መንጦላዕተ ሥጋ ሰብእ መዋቲ ፤ ወረደ ዲበ ምድር ፤ ወአንሶሰወ ውስተ ዓለም በበሕቅ ልሕቀ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ።

### ትርጉም ።

የመጀመሪያው ቃል ይህ ቃል ነው ፤ እሱም የእግዚአብሔር ቃል (ወልድ) ነው ፤ ቃል ሥጋ ሆነ (ተዋሐደ) ከሰማያት ከሥልጣናት በላይ የሆነ የማይዳሠሥና የማይነካ ረቂቅ አምላክ በሥጋ ተዳሠሠ ፤ ሟች የሆነ የሰውንም ሥጋ መጋረጃ አደረገ በምድር ላይ ወረደ ፤ በዓለምም ተመላለሰ በየጥቂቱ አደገ ፤ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ።

### ፲፬ኛ አቡን ።

ነአምን በአብ ፤ ወነአምን በወልድ ፤ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ፤ እማርያም ዘተወልደ አፍቂሮ ኪያነ መጽአ ኀቤነ ዘነቢያት ሰበኩ ለነ ፤ በዮርዳኖስ ተጠምቀ ከመ ይፈጽም ኵሎ ሕገ ወአስተርአየ ገሀደ ።

### ትርጉም

በአብ እናምናለን ፤ በወልድም እናምናለን ፤ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን ፤ ነቢያት ስለሱ የሰበኩልን እኛን ወዶ ፤ ወደእኛ መጣ ፤ ከማርያም ተወለደ ፤ ሕግን ይፈጽም ዘንድ ወይም ሕግን ፈጽሞ ፤ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፤ በግልጥም ታየ ።

### ፲፮ኛ ዓራራይ እስመ ለዓለም ፤

እምሰማያት ወረደ ፤ ወእማርያም ተወልደ ፤ ከመ ይሥዓር መርገማ ለሔዋ ዲበ ዕፅ ተሰቅለ ፤ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ዘነቢያት ሰበክዎ ፤ ወአስተርአየ ገሀደ ።

### ትርጉም ፤

ነቢያት የሰበኩት አምላክ ከሰማይ ወረደ ፤ ከማርያም ተወለደ ፤ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፤ በግልጽም ታየ ፤ የሔዋንንም መርገም ይሽር ዘንድ ፤ በእንጨት ላይ ተሰቀለ ።

### ፲፰ኛ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ የሚያነበው የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ቲቶ ፫.፬ ፰ ፤

ሰውን የሚወድ የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነት በተገለጠ ጊዜ ፤ ጽድቅ በመሥራታችን አይደለም ፤ በቸርነቱ ነው እንጂ ፤ ፪ኛ ልደት በሚሆን በጥምቀት ፤ በመንፈስ ቅዱስም በመታደስ አዳነን ።

### ፲፱ኛ ፤ ንፍቁ ዲያቆን የሚያነበው የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት ፩ ዮሐ ፭፡፭–፰

ይህን ዓለም ድል የሚነሳው ማነው ? ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያምን ነው እንጂ ፤ በውኃና በደም በመንፈስም እንደመጣ ፤ በውኃ ብቻ አይደለም ፤ በውሀም በደምም በመንፈስም ነው እንጂ ፤ የእውነት መንፈስ እንደመሆኑ የሚ



መሰክር ነው። የሚመሰክሩ መንፈስ ውኃና ደም እነዚህ ሦስቱ ናቸውና ፤ ሦስቱም አንድ ናቸው ።

### ፳ ንፍቁ ቄስ የሚያነበው የሐዋርያት ሥራ ም ፲ ፴፬-፴፯ ።

ጴጥሮስ አፉን ገልጦ አለ ፡ እግዚአብሔር በሰው ፊት እንደማያደላ በእውነት አስተዋልሁ ። ነገር ግን ከሕዝቡ ሁሉ እሱን የሚፈራና ቅን ነገርን የሚያደርግ ቢኖር ፤ በእሱ ዘንድ የተወደደ ነው ። ወደ እሥራኤል ልጆች የተላከው ቃል የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን የሚሰብክ ነው፤ ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ፣ ከገሊላ ጀምሮ በይሁዳ ሁሉ የሚሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ ።

### ፳፩ኛ የቅዳሴ ምስባክ

ርእዩከ ማያት እግዚኦ !
ርእዩከ ማያት፤ ወፈርሁ ፤
ደንገጹ ቀላያተ ማያት ፤ ወደምፀ ማያቲሆሙ ።

### ትርጉም

አቤቱ ! ውኃዎች አዩህ ፤ አይተውህም ፈሩ ፤ የውኃ ወንዞችም ደነገጡ ፤ ውኃዎቻቸውም ተሰሙ ።

### ፳፪ኛ ወንጌል ሉቃስ ም፡ ፫ ፳፩—፳፪ ፤

ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ፡ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ ። እሱም ሲጸልይ ፡ ሰማይ ተከፈተ ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አካል አምሳል ወርዶ፤ በላዩ ተቀመጠ ። ከሰማይም የምወድህ ፤ ደስታዬንም የማገኝብህ ልጄ አንተ ነህ የሚል ድምፅ መጣ ። የኢየሱስም ዕድሜው ፴ ዓመት ያህል ነበር ።

### ፳፫ኛ ዝማሬ ፤

ርእይዎ ኖሎት አዕኰትዎ መላእክት ለዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል፣ ዮም ሰማያዊ በኀል ሰከበ ።

ሙሴኒ ይቤ ዘተናገሮ በዐምደ ደመና ፤ ርኢክዎ ፤ ወስዕንኩ ጠይቆቶ ፤ ዮም ሰማያዊ በማይ ተጠምቀ ። ማርያምኒ ትቤ አንተ ፆረቶ በከርሣ ፤ ርኢክዎ ወስዕንኩ ጠይቆቶ ፤ ዮም ሰማያዊ በኀል ሰከበ።ዮሐንስኒ ይቤ ዘአጥመቆ በዮርዳኖስ ርኢክዎ ወስዕንኩ ጠይቆቶ ዮም ሰማያዊ በማይ ተጠምቀ። እንድርያስኒ ይቤ ዘነገደ ባሕረ ምስሌሁ ፡ ርኢክዎ ወስዕንኩ ጠይቆቶ ፤ ዮም ሰማያዊ በኀል ሰከበ ።

በ፪ዔ ዓሣ ወበ፭ቱ ኅብስት አጽገቦሙ ኢየሱስ ለ፶፻ት ዮም ሰማያዊ በማይ ተጠምቀ ፤ በበሕቀ ልሕቀ ፤ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ።

### ትርጉም ።

ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደውን (ሕፃን) እረኞች አዩት፣ መላእክት አመሰገኑት ፡ ሰማያዊው (አምላክ) ዛሬ በበረት ተኛ ፤ ዛሬ በውኃ ተጠመቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዓምደ ደመና (በደመና ምሰሶ) የተነጋገረው ሙሴም አይቼው ነበር ፤ ልጠይቀው ግን አልቻልሁም አለ ። በሆዷ የተሸከመችው ማርያምም አይቸው ነበር ፤ ግን ልጠይቀው አልቻልሁም አለች ። በዮርዳኖስ ያጠመቀው ዮሐንስም አየሁት ፤ ልመረምረው ግን ፤ አልቻልሁም አለ ።



በሁለት ዓሣና በ፭ እንጀራ ፭ሺ ሕዝብ አጠገበ ።

ከእሱ ጋር በባሕር በመርከብ የሔደው እንድርያስ ...



ጠይቄ ልረዳው ፤ አልቻልሁም አለ ፤ እሱ ኢየሱስ ነው በሁለት ዓሣና በ፭ት እንጀራ ፭ቱን ሺሕ ሕዝብ ያጠገባቸው ። እሱ በየጥቂቱ አደገ ፤ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ።

## ፳፬ኛ በባሕር የሚነበቡ የሐዲስ ኪዳን ምንባባትና ምስባክት

### ሀ ምስባክ

ቃለ እግዚአብሔር ላዕለ ማያት ፤
አምላከ ስብሓት አንጐድጐደ ፤
እግዚአብሔር ላዕለ ማያት ብዙኃ ።

### ት ር ጕ ም

የእግዚአብሔር ቃል በውኃዎች ላይ ነው ፤
የክብር አምላክ ያንጎደጕዳል ፤
እግዚአብሔር በብዙ ውኃዎች ላይ ነው ።

### ለ. ወ ን ጌ ል

ከቅኔ ማኅሌት የተነበበው የማቴዎስ ወንጌል ም፡ ፫ ተመልሶ ይነበባል ።

### ሐ ም ስ ባ ክ

በቅዳሴ ጊዜ የተባለው ርእዩከ ማያት የሚለው፤ ተመልሶ ይነበባል ።

### መ ወንጌል

ማርቆስ ም፡ ፩ ቀ፡ ፱—፲፪ በዚያ ወራትም ኢየሱስ ከናዝሬት ከገሊላ መጣ ከዮሐንስ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ።

ከውኃም ሲወጣ ፤ ሰማዮች ሲከፈቱ መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ ሲወርድ አየ ከሰማይም የምወድህ ፤ ደስታዬንም የማይብህ ልጄ አንተ ነህ የሚል ድምፅ መጣ።

### ሠ፡ ምስባክ

ከቅኔ ማኅሌት የተባለው «ባሕርኒ ርእየት» የሚለው ተመልሶ ይነበባል ።

### ረ፡ ወንጌል

በቅዳሴ ጊዜ የተነበበው ሉቃስ ም. ፫, ቀ. ፳፩—ፍ ያለው ንባብ ነው ።

### ሰ ዲያቆኑ የሚያነበው የጳውሎስ መልእክት

፩ ቆሮንቶስ ም. ፲፪ ቀ. ፲፫—እኛም ሁላችን በ፩ ሥጋ ፩ ነፍስ በመሆን፤ ተጠምቀናል ፤ አይሁዳዊም ፤ አረማዊም፤ ጌታም ፤ ቤተ ሰብም ብንሆን ሁላችን አንድ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል ።

### ቀ ንፍቅ ዲያቆኑ የሚያነበው የጴጥሮስ መልእክት ።

፩ኛ. ጴጥሮስ ፫፡ ፳፩ እኛም ዛሬ በኖኅ ምሳሌ በጥምቀት ያድነናል ፤ ሥጋን ከዕድፍ በማንፃት አይደለም በጎውን ሥራ ያስተምረን ዘንድ ነው እንጂ ።

www.ethiopianorthodox.org

## በንፍቅ ቄስ የሚያነበው የሐዋርያት ሥራ ።

የሐዋ ሥራ ም. ፲፱ ቍ. ፪—፯ ። ጳውሎስ በኤፌሶን የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት በአመናችሁ ጊዜ ፤ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን ? አላቸው ። እነሱም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳን ፤ አልሰማንም አሉት ። እርሱም እንግዲያው በምን ተጠመቃችሁ ? አላቸው ። እነሱም በዮሐንስ ጥምቀት አሉት ። ጳውሎስም ዮሐንስስ ከሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየሰበከ ፤ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው ። እነሱም ይህን በሰሙ ጊዜ ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ። ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው ።

## ተ. ምስባክ ።

ምንተ ክንኪ ባሕር ዘጐየይኪ ፤
ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባዕከ ድኅሬከ ፤
አድባር አንፈርዓፅክሙ ከመ ሐራጊት ።

## ትርጉም

ባሕር ምን ሆነሽ ሸሸሽ ?
አንተስ ዮርዳኖስ ወደ ኋላህ የተመለስኸው ምን ሆነህ ነው ?
ተራሮች እንደ ጊደሮች ዘለላችሁ ።

## ኀ ወንጌል

ዮሐ. ም. ፩፡ ቍ፡ ፯–፲፰ ። ስሙ ዮሐንስ የሚባል ፤ ከእግዚአብሔር የተላከ አንድ ሰው ነበር ።እሱ ፤ ሁሉ በርሱ ያምን ዘንድ ስለ ብርሃን ሊመሰክር ለምስክርነት መጣ ። እሱ ብርሃን አልነበረም ፤ ነገር ግን ለብርሃን ሊመሰክር ተላከ ። ወደ ዓለም የመጣው ለሰው ሁሉ የሚያበራ ዕውነተኛ ብርሃን ነበረ ። በዓለም ነበረ ፤ ዓለሙም በርሱ ሆነ ፤ ዓለምም አላወቀውም ። ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም። የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ በስሙ ለሚያምኑ ፤ ለተቀበሉት ሁሉ ግን ሥልጣን ሰጣቸው ። ከደም ወገን ፤ ከሥጋ ፈቃድም ፤ ከሰው መዋደድም ያልሆኑ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ቃልም ሥጋ ሆነ ፤ በእኛም አደረ ፤ ክብሩንም አየን አንድ እንደ መሆኑ ክብር ከአብ ፤ ጸጋ ዕውነትም የመላበት ። ዮሐንስ ስለሱ መሰከረ ፤ «ከኔ በኋላ የሚመጣው ፤ እሱ በፊቴ ሆነ ፤ ከኔ ከፊት ነበርና ያልሁት ይህ ነው» እያለም ጮኸ ። ከምላቱም እኛ ሁላችን በጸጋ ፈንታ ጸጋን ወሰድን ። አሪት በሙሴ ተሰጥቶናልና ጸጋና ዕውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን ።


## ፳፫ኛ ከባሕር መመለሻ ሰላም

የም ፍሥሓ ክነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ ወበእንተ ጥምቀቱ ፤ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ኅዲጎ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ ቆመ ማዕከለ ባሕር ገብአ ወወጽአ በሰላም ።



## ትርጉም

ስለክርስቶስ ልደትና ስለ ጥምቀቱ ዛሬ ደስታ ሆነ ፤ ቅድመ ዓለም የነበረ ፤ ዓለ



የባለተራው የታዕካ ነገሥት በአታ መዘምራን ሲያሸበሽቡ ።

ምን አሳልፎ የሚኖር ዘለዓለማዊ አምላክ ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ ፤ በባሕር መካከል ቆመ ፤ ተመልሶም በሰላም ወጣ ።

ከዚህ በላይ ከዋዜማ እስከ ሰላም ያለው የበዓለ ጥምቀት ፀዋትወ ዜማ በተራው ተዘጋጅቶ ከክንፈ ገብርኤል አልታዩ ከግዕዝ ወደአማርኛ ተተረጐመ ።

www.ethiopianorthodox.org